
# ትንሣኤ



በምድረ ጅቡቲ የምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ፤

የነሐሴ ፡ የመስከረምና ፡ የጥቅምት ወራት
፲፱፻፹፪ ዓ·ም

ቁጥር ፩፻፴፰



በሰሜን ሀገረ ስብከት የቆጋ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ፤

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ፍሬ እንዲተረጎሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ሰሜን ወርቅ በዛብን
ም አዘጋጅ መ ክንፈ
ርግብ ማርቆስ



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡


# ማ ው ጫ

## አርእስት


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ርእስ አንቀጽ (ርእስ ዓውደ ዓመት) | ፪ |
| ባየነው እንመሰክራለን | ፬ |
| ✓ ዜና ሊቃውንት | ፭ |
| የቤተ ክርስቲያን ታሪክ | ፯ |
| የማኅበረ ሥላሴ ገዳም ታሪክ በአጭሩ | ፱ |
| ዜና ዕረፍት | ፲፩ |
| ቅዱስ ሩፋኤል ለጦብያ | ፲፪ |
| ዘመን ሲለወጥ | ፲፭ |
| የአባ ገብረ ጻድቅ በሻህ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ | ፲፯ |
| ቅዱስ ዮሐንስ | ፲፱ |
| መስቀል ኃይላችን ነው | ፳ |
| የቆጋ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ታሪክ | ፳፩ |
| ጻዕዳ አምባ ሥላሴና ታሪኩ | ፳፪ |
| ወርኃ ጽጌያት ድንግል ማርያም በመንፈቀ ሌሊት | ፳፬ |


# ደብዳቤዎች

ለስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፤

በቅድሚያ በክርስቶስ ሰላም ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከዚህም ጋር በማያያዝ ስለቀዳሚት ሰንበት አከባበር በመጽሔትና በጋዜጣ የተለያየ አቀራረብ ሆኖ ስላገኘሁት እውነተኛው የትኛው እንደሆነ ለመረዳት የሚከተለውን ጥያቄ አቀርባለሁ ።

ይኸውም ፩ኛው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ቀዳሚት ሰንበት የእግዚአብሔር ሕግ እንደመሆንዋ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የተከበረች ናት በማለት ቁጥሩ ፪፻፹፪ በሆነውና በሚያዝያው ወር ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ታትሞ በወጣው ድምፀ ተዋህዶ ጋዜጣ አስተላልፈዋል ።

፪ኛ/ ደግሞ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ቀዳሚት ሰንበትን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሽሮታል በማለት ቁጥሩ ፩፻፳ በሆነውና በኅዳር ወር ፲፱፻፹ ዓ/ም ታትሞ በወጣው ትንሣኤ መጽሔት ገልጸዋል ።

ስለዚህ እኔ ልረዳው የምፈልገው የድምፀ ተዋህዶ ጋዜጣ እንዳልተሻረች ሲያስረዳ የትንሣኤ መጽሔት ግን እንደ ተሻረች ይገልጻል ። እውነተኛና ሕዝቡ መያዝ የሚገባው የትኛውን ነው?

አቶ ታደሰ ረታ ጐንደር ክፍለ ሀገር

መልስ

አቶ ታደሰ ረታ ቁጥር ፪፻፹፪ በሆነው ድምፀ ተዋሕዶና ቁጥር ፩፻፳ በሆነው ትንሣኤ መጽሔት ታትሞ የወጣው የተለያየ መስሎዎት እንጂ የተለያየ አይደለም ።

፩ኛ· ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ቀዳሚት ሰንበት የእግዚአብሔር ሕግ እንደመሆንዋ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የተከበረች ናት ማለታቸው ትክክለኛ ነው ይኸውም በብሉይ ኪዳን አክብር ሰንበቶ ለእግዚአብሔር አምላክከ (የአምላክህ የእግዚአብሔርን ሰንበት አክብር ዘጸአ·ም·፳ ቁ ፰ ተብሎ የተነገረላት ለቀዳሚት ሰንበት ሲሆን በሐዲስ ኪዳንም እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ አታልፍም ተብሎ የተነገረውም ስለ ቀዳሚት ሰንበት እንደሆነ በግልጽ ያመለክታል ከአውርቱ ቃላትም አንዲቱ ቀዳሚት ሰንበት ናት አጻጻፉ ትክክል ነው።

፪ኛ· ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ቀዳሚት ሰንበትን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሽሮታል ብለው የተናገሩት ጥቃቅኑን ነገሮች ሁሉ እንደ ሻራቸው ሲያመለክቱ ነው ለምሳሌ ኢትጥአምን ኢትልክፍን፡ ርኩስ እስከ ሥርክ የሚሉትን ቃላት ሁሉ አሁንም ሽሯቸዋል እጅንና እግርን አጣምሮ መዋል እንደማይገባ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል መልስ ሰጥቶበታል ደቀ መዛሙርቱ እሸት ቀጥፈው በበሉ ጊዜ ለምን በሰንበት እሸትን ቀጠፉ ተብለው ቢከሰሱ ዳዊት በተራበ ጊዜ ያደረገውን አላነበባችሁምን ሲል መልስ እንደሰጠበት በማቴ· ወንጌ ፲፪ ፩—፰ ተገልጿል ።

በተጨማሪም በሰንበት ቀን እጅህንና እግርህን አታንሣ ተብሎ ተጽፎ የነበረውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሻረው ለማወቅ በሰንበት ቀን መልካሙን ሥራ መሥራት ተፈቅዷል ብሏል ማቴ ፲፪ ፡ ቁ·፲፪

እንዲህ ማለት ለማረስ ለመቆፈር ሳይሆን ድውይን ለመጠየቅ በሽተኛውን ለማስታመምና እሥረኛውን ለመጠየቅ ማለት ነው ። ስለዚህ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስም ሆኑ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ያስተላለፉት አባታዊ ትምህርትና ስለ ቀዳሚት ሰንበት የሰጡት አስተያየት የተለያየ መስሎ ታየዎት እንጂ የተለያየ አይደለም የተለያየም እንዳይደለ የተጠቀሱትን ጥቅሶች በጥንቃቄ ይመልከቱ ምሑረ ኦሪቱና የሐዲስ ኪዳን ምርጥ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም በኦሪት የነበሩት ቃላት አምሳል መርገፍና ጥላዎች እንደ ነበሩ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል ።

እንግዲህ "በመብል ፣ ወይም በመጠጥ ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ ሲል አብራርቶ ተናግሯል ። ቈላ ፪፣፲፮ ።

ከዚህ ላይ በቁጥር ፲፮ ላይ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ ያለውን ማስተዋል ይገባል ።

ስለዚህ ጥቅሶቹን ተመልክተው ለምን እንደተጠቀሱም መርምረው እንዲረዱ እናሳስብዎታለን ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ




www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ርእሰ ዓውደ ዓመት የአዲስ ዘመን መጀመሪያ

በኢትዮጵያ ያለፈው ዓመት አልቆ የሚተካው የሚጀመርበት መስከረም አንድ ቀን እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት ርእሰ ዓውደ ዓመት የሚል ሥያሜ ተሰጥቶታል ። ዘመን ሲያልፍ ዘመን ይተካል ትውልድም ሲያልፍ የሚተካው ትውልድ ነው ለኀልፈትና ለውላጤ የተፈጠረ ፍጡር ሁሉ ወቅትና ጊዜ አለው በዚያው በተሰጠው ዘመን ሁሉም ሥራውን ያከናውናል ። አከናውኖም ያልፋል ያለ ሥራ የተፈጠረ ፍጡር የለምና ።

እግዚአብሔር አምላክ ፍጥረታትን ፈጥሮ ሲፈጽም "ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ዘሠናይ" እግዚአብሔር አምላክ የፈጠረው ፍጥረት መልካም እንደሆነ አየ ይላል ዘፍ. ፩ ፡ ፴፩ ይህም የሚያስረዳው የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ያለ አገልግሎት የተፈጠረ አለመሆኑን ነው ። በሰው ዘንድ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጡራን መካከል የሚወደዱና የሚጠሉ ሊኖሩ ይችላል ። በአምላክ ዘንድ ግን ሁሉም ፍጥረት የተወደዱ ናቸው ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያስረዳ "እግዚአብሔር የፈጠረው ሥነ ፍጥረት ሁሉ ያማረና የተወደደ ነው ምንም የሚጣል የለውም" ብሏል ፩ኛ ጢሞቴዎስ ፬.፬ የሐ.ሥራ.፲.፲፭

እግዚአብሔር ፈጥሮ አይጥልም አይረሳም አይዘነጋም ፍጥረቱን ሁሉ በምግብ በጤና ወዘተ. ተንከባክቦ ጠብቆ እስከ ተወሰነለት ጊዜ ያኖረዋል ፡ በይበልጥ ለሰው የሚያደርገው ልግሥና የሚሰጠው ጸጋ ጥበብ ከሌላው ፍጥረት የላቀ ነው በምግብ ፡ በልብስ ፡ እንደይቸገር ከማድረጉም ሌላ ዘመኑን የሚሠፍርበትና የሚቀጥርበትም አዘጋጅቶ እንዲጠቀም ማስተዋልን ሰጥቶታል ፡ ስለዚህ ሰከንዱን በደቂቃ ደቂቃውን በሰዓት ሰዓቱን በቀን ቀኑን በሳምንት ሳምንቱን በወር ወሩን በዓመት እያጠቃለለ ምድራዊ ሕይወቱን ከማገባደድ ይደርሳል ። ከዚህም የተነሣ ከላይ እንደተገለጸው አንዱ ዓመት አልፎ ሌላው ሲተካ ርእሰ ዓውደ ዓመት የዓመት መጀመሪያ ይባላል ።

በኢትዮጵያ አመዳደብ ዘመናቱ አራቱን ክፍላተ ወንጌል በጻፉት በ፬ቱ ወንጌላውያን ስም እንዲጠሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ወስነዋል ። ወንጌላውያኑም ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ ናቸው። ከእነርሱም ማቴዎስና ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል ሲሆኑ ማርቆስና ሉቃስ ከሰባ ሁለቱ አርድዕት ናቸው ። በኢትዮጵያችን የዓመቱ መጀመሪያ የሚጠራው ቅዱስ ዮሐንስ እየተባለ ነው ወንጌላውያኑ ግን በየዓመቱ ይፈራረቃሉ ድርሻቸውም ማቴዎስ ፡ ማርቆስ ፡ ዮሐንስ ፲፻፷፭ ቀን ሲሆን የሉቃስ ፲፻፷፮ ቀኖች ይሆናሉ በዓመቱ መጀመሪያ ቀን በቤተ ክርስቲያን በዕውቀት ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ሊቃውንት የበዓላትና የዓጽዋማትን ቀኖች ለምእመናን የሚያሰሙበት ዕለት በመሆኑ "ርእሰ ዓውደ ዓመት ዮሐንስ ወላደ መጥቅዕ ወአበቅቴ" ዮሐንስ የዓመቱ መጀመሪያ የመጥቅዕና የአበቅቴ አስገኝ ነው ተብሎ ተጽፏል ።

መጥቅዕ የበዓላትና የአጽዋማት ማውጫ ሲሆን አበቅቴ ደግሞ ከሠርቀ መዓልትና ከሕፀፅ ጋር ተደምሮ የሌሊት ማውጫ ነው በዚህ ርእሰ ዓውደ ዓመት ዕለት ልብ አድርገን ልንመለከተው የሚገባ ዓቢይ ነገር ለለ ይኸውም ከዓመት እስከ ዓመት የሠራነውን ሥራ ነው ።

ዘመን ፍጡራንን ሁሉ የሚያታግል የትግል መስክ ነው እርስ በእርሳቸው የሚታገሉ ሰዎች ሁለቱም የድል ባለቤቶች ሊሆኑ አይችሉም ፡ አንድ ጊዜ የማሸነፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ የመሸነፍ ዕድል ሊገጥማቸው ይችላል ግን አንድ ጊዜ ተሸነፍኩኝ ብሎ ተስፋ መቁረጥ ተገቢ አይደለም ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔርን ረዳትና አጋዥ አድርጉ ለመልካም ነገር መጣርና መታገል ያስፈልጋል ።

ሰው በዚህ ዓለም ጠንክሮ ካልታገሉ ሥጋዊ ኑሮን አሸንፎ በሰላምና በደስታ ለመኖር አይቻልም ። እጅን አጣምሮ በሕይወተ ሥጋ እስከ ለለ ድረስ ጠንክሮ የመሥራት ግደታ ለለበት ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ አገርን ኮርተም ቢመለከቱት ተሐድሶ አይገኝም ብልጽግናንም አያጉናጽፍም ።

ዘመን የሥራን የንቃትናን የትጋትን የፍቅርንና የሰላምን ተሳትፎ በብርቱ ይጠይቃል ዘመን አልፎ ከሄደ በኋላ አይመለስም አስቀድሞ የተዘጋጀ ብቻ አብሮት ለመራመድ ይችላል ።



በዘመን የማይለወጥ ነገር የለም ዛሬ ያገኘው ነገ ያጣል ዛሬ ያጣው ከነገ ወዲያ ያገኛል ። ዛሬ በጽኑዕ የታመመው በሽተኛ ጥቂት ቀን ሰንብቶ ሊፈወስ ይችላል ። ዛሬ ጤነኛ ነኝ የሚለው ከጊዜ በኋላ ደግሞ በደዌ ዳኛ ባልጋ ቁራኛ ተይዞ ሊጨነቅ ይችላል ። እንዲህ ዓይነቱ ችግር በደረሰ ጊዜ ዘመን አመጣብኝ ብሎ በዘመኑ ማመካኘት አይገባውም ዘመን የመስጠትና የመንሣት የማዳንና የማሳመም ሥልጣን የለውምና ሁሉም ያለ ፈጣሪ ሊፈጸም አይችልም ። ዘመናትም ሆኑ ሌሎች ፍጥረታት ያለእግዚአብሔር ፈቃድ የደስታም ሆነ የችግር ምክንያቶች ለመሆን አይችሉም ፡ ያለፈው ዓመት በጅቷቸው በዓውደ ዓመቱ የሚደሰቱ ሲኖሩ ዘመኑ ከፍቶባቸው እያዘኑ ያለፈውን ዘመን መልሰህ አታምጣብን ፡ የሚመጣውን ዘመን የደስታ አድርግልን በማለት እግዚአብሔር አምላክን የሚማጸኑ አሉ ።

አሳቡ መልካም ነው ሁሉም ያለእርሱ ፈቃድ አይሆንምና ለደስታም ሆነ ለኀዘን ለብልጽግናም ሆነ ለድኅነት ምንጩ ዘመን እንደሆነ አድርገው የሚናገሩ ፡ አንዳንድ ሰዎች አይታጡም ።

ዘመን ግን ታዛዥ እንጂ አዛዥ አይደለም ዘመን ለሰው ልጆች የሥራ መሥሪያ እንዲሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠ በመሆኑ በሰው ላይ መጥፎ ነገርን እንዲያመጣ የተፈጠረ አይደለምና ።

"ያለፈው ዘመን አልሆነኝም ይህ ዘመን ግን ይሆነኛል በይበልጥ ደግሞ ከርሞ የሚመጣው ከፍሊ ነው" እያሉ ራሳቸውን በራሳቸው የሚደልሉ አንዳንድ ሰዎች መኖራቸው አያጠራጥርም ይህ ሁሉ ከንቱ አስተሳሰብ ስለሆነ እግዚአብሔርን ረዳት አድርጉ ሳይጠራጠሩ ጠንክሮ መሥራት ከማንኛውም ችግር ሊያድን ይችላል ።

አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱ ሲተካ ባለፈው ዘመን የሠሩትን ሥራ ማስተዋል ያስፈልጋል የሰነፈ ቢኖር ባለመሥራቱ ተጸጽቶ ለወደፊቱ ጠንክሮ ለመሥራት ታጥቆ መነሣት አለበት ክፉ ሥራ ሠርቶ ከእግዚአብሔር አንድነት የተለየ ቢኖርም በንስሐ ታድሶ ወደፈጣሪው ለመቀረብ መዘጋጀት ይኖርበታል ርእሰ ዓውደ ዓመት ተብሎ የተሰየመውን የዓመት መጀመሪያ ስናከብር አዲሱን ዘመን የሰላም የፍቅር የበረከት የጥጋብ የደስታ እንዲያደርግልን እግዚአብሔርን በመለመን ነው ።

ዘመኑን የተጣላ የሚታረቅበት የታመመ የሚፈወስበት ያጣና የተቸገረ ሠርቶ የሚያገኝበት የደከመ የሚጠነክርበት ያድርግልን አሜን ።

## የቆጋ ኪዳ... ገዳም

(ከገጽ ፳፩ የዞረ)

ስቲያኖች ጭፍጨፋና የገዳማትና የአድባራት ማውደም ዘመቻ ምክ ንያት ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍ ሎች በተለይም ከወሎ ከአማራሳይ ንት ከሸዋ ከደብረ ብርሃን አያሌ መነኮሳትና መነኮሳይያት ተሰደው ቆጋ ኪዳነ ምህረት ገዳም ገብተ ዋል ፡ አያሌ የበቁ አባቶች እንደነአ ቡነ መፆረ ድንግል በቆጋ ገዳም ኑረውበታል ።

ከላይ በአጭሩ እንደተገለጸው የቆጋ ኪዳነ ምህረት ገዳም ጥንታዊ ሲሆን በክርስቲያኖችም ዘንድ የታ ወቀና የተከበረ ነው እንዲታወቅና ዝነኛም ያደረገው የማኅበሩ መነኮ ሳት ጠንካራ ሥርዓት ነው ፡ ቆጋ ኪዳነ ምህረት ገዳም የአንድነት ነው መነኮሳቱም ፡ በአንድ መም ህር (አበምኔት) ታዝዘው የሚያ ድሩ ናቸው አባላቱ ሁሉ ከልሒቅ እስከ ደቂቅ በማረስ በመቆፈር በማ ምረት በማብሰል በልዩ ልዩ የገዳም አገልግሎት ተሠማርተው ያገለግ ላሉ ፡ በተለያዩ መንፈሳዊና ማኅበ ራዊ አገልግሎት ሲሠሩ ከዋሉ በኋላ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ምግብ ይመገባሉ ።

ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ላይ ደወል ሲደወል መነኮሳቱ ሁሉ በአንድ ቤት ውስጥ ተሰብስበው ይመገባሉ ከምግብ በኋላም የአንድነት ጸሎ ትና ምህላ ያደርጋሉ ፡ በገዳሙ ውስጥ ጸሎትና መንፈሳዊ አገልግ ሎት ምን ጊዜም አይቋረጥም ቢት በእኩለ ቀን በዘጠኝ ሰዓት በአሥራ ሁለት ሰዓት ማስታኰት ግብረ ሌሊት ኪዳን ስግደት ጸሎት በገ ዳሙ የማይቀርና የማይታጐል ዕለ ታዊ ተግባር ነው በዓላት በአልሆኑ ቀናት ዘወትር ከ፫ ሰዓት እስከ ፱ ሰዓት የገዳሙ አባላት መናንያን በልዩ ልዩ የሥራ መስክ ይሠማ ራሉ ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ ደግሞ የጸሎት የስግደት የምህላ ጊዜ ነው።

<u>ገዳሙ በአሁኑ ጊዜ</u> በአሁኑ ወቅት በዚህ ታላቅና ዝነኛ ገዳም ከመቶ ሰላሳ በላይ የሚሆኑ መነኮ ሳት ይገኛሉ ቆጋ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ታሪካዊና ጠንካራ ሥርዓት ያለው ገዳም ነው ስለሆነም መናን ያኑ ሁሉ በተለያዩ የማምረትና የአገልግሎት ተግባራት ላይ ተሠ ማርተው የጋራ አስተዋጽኦ ስለሚ

(ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

# “ባየነው እንመሰክራለን”
## (ዮሐ·፫·፲፩)

ለማንኛም ምስክርነት ለመስ ጠት በዐይን ማየት በትክክል መረዳት በግድ ያስፈልጋል ፡ ሰማሁ ብሎ ወይም ግምት ወስዶ መናገር ማመስገንም መንቀፍም ለሰው ልጅ ሁሉ ከቶ ተገቢ አይደለም ፡ እውነተኛ ምስክር የሚባለው በትክክል አይቶ ሲናገር የዐይን ምስክር ሆኖ ሲገኝ ነው ።

የትንሣኤን በዐል ጅቡቲ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተገኝቼ እንዳከብር ከመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽቤት ታዝዤ ሄጄ በዚያ ውየ ነበር ፡ በዚያም እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱን በትክክል የገለጠበት ተአምራታዊ ሥራውን አሁንም የሚቀጥልበት የሊቀ ጳጳሱን የአቡነ ኤልያስንና የጅቡቲን ሕዝበ ክርስቲያን ኅብረታዊ አስተዋጽኦን የሚያስረዳ የምስክርነት ሐውልት የሆነውን የምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንንና ሙሉ ድርጅቱን ለማየት ችያለሁ ። ቤተ ክርስቲያን ይሠራል ተብሎ ባልታሰበበት በዚያ ቦታ በሕንፃው ጥንካሬ በውበቱ ዐይንን የሚማርክ ፡ የሁሉን ስሜት የሚስብ ታላቅ ሕንፃ በተፋጠነ ሁኔታ ተፈጽሞ በሥራ ላይ መዋሉ የሊቀ ጳጳሱን ከፍተኛ ጥረት ፡ የሕዝቡን ፍጹም ተባባሪነት በግልጽ ያሳያል ይመሰክራልም ።

ተገቢውን ሰው በተገቢው ቦታ ማዋል እንደዚህ ያለ ውጤትን ለማስገኘት ይበጃል ፡ በዚያ ቦታ እንደ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ያለ ተጣጣሪ ሊቀ ጳጳስ ባይሾም እንኳን ቤተ ክርስቲያኑ አምሮ ተሠርቶ ፍጻሜ አግኝቶ መታየት ቀርቶ መቃረቢያም ሊኖረው ባል ቻለም ነበር ። በረሀብና በጥም የማይፈቱ ፡ በቃጠሎው (በሙቀቱ) የማይሰለቹ የጀመሩትን ከግብ ሳያደርሱ ዕረፍትን ለማድረግ የማይፈቅዱ አባት በመሆናቸው ሕዝበ ክርስቲያኑ አምኖባቸው እንደ እርሳቸው አብሮ እየታመመ ፡ ገንዘቡን ፡ጉልበቱን ፡ ዕውቀቱን በማውጣቱ ይኸን ይመስላል ፡ ይኸንም ያከላል ተብሎ ግምት ለመስጠት የሚያዳግት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራትና በቶሎም ፍጻሜውን ለማየት በቃ ። ባየነው እንመሰክራለን ብዬ በርእሱ እንደገለጥኩት ያን ታምራታዊ ሥራ አይቶ ተመልሶ እንዲሁ ዝም ማለት እውነቱን ለመመስከር ለሌላውም ለማስረዳት አላዋቂነት ነው ፡ እንዲያውም እንደኔው ሁሉም ዕድል ገጥሞት በአገልግሎትም በጉብኝትም ሄዶ ቤተ ክርስቲያኑንና የሕዝቡን ኅብረት እንዲያይና እንዲመሰክር እግር መንገዴን እጋብዛለሁ ።

የጅቡቲ ሕዝበ ክርስቲያን ያንን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሠራን እንግዲህ እንረፍ አላሉም ነገር ግን አሁንም ቤተ ክርስቲያኑ የሚደገፍበትን አገልግሎቱ ተጠናክሮ የሚካሄድበትን በመሥራት አስተዋጽኦም በማበርከት ላይ ይገኛል።

ለምሳሌ:— እኔ ከሔድኩበት ጊዜ ጀምሮ የብዙዎች ምእመናን ሸክም እንደሆንኩኝ ቢሰማኝም ሕዝቡ ግን በጎ አድራጎት ልማዱ ስለሆነ ትንሽም ቅር አላለውም ፡ ያውም የጊዜው ሁናቴ በዚያ አገር ተፈጥሮበት የነበረ ጊዜ ቢሆንም ሕዝቡ ለበጎ አድራጎት የተቆጠበ አይደለምና ተገቢውን አገልግሎት በሚገባ ፈጽሟል ። ይኸ የኔ በዚያ መገኘት በአንድ በኩል ሲያስደስተኝ በሌላ በኩል ደግሞ ሲያሳፍረኝ ነበር ፡ ምክንያቱም አንዳንድ ክርስቲያኖች በኔ መሔድ ሳይረኩ ሊቀ ጳጳሳቸው በመቅረታቸው ማዘናቸው ይታየኝ ነበርና ፡ ነገር ግን ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በሕዝቡ ላይ ያላቸውን ተወዳጅነት ስመለከት በጣም ደስ ይለኝ ነበር ።

ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በበዓለ ትንሣኤ ጊዜ በጅቡቲ ያልተገኙበት ምክንያት የምሥራቅ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ እርሳቸው እንደመሆናቸው በኬንያ (ናይሮቢ) በተቋቋመው ቤተ ክርስቲያን በተራው አገልግሎት ለመስጠት በዚያ መገኘት ስለነበረባቸው ነው ።

በጅቡቲ የሚገኘው ሕዝበ ክርስቲያን የሀገር ፍቅር የክርስትናም ክብር በጣም ጎልቶ የሚታይበት በመሆኑ ስመሰክር ጠቅላይ ቤተ ክህነቱ በየጊዜው ደህና አገልግሎት የሚሰጡ ካህናት ቢልክላቸው የበለጠ የሚደሰቱ መሆናቸውን እገልጣለሁ ።

ቤተ ክርስቲያኑ በዚያ አገር በመቆሙ አገልግሎቱም በተፈላጊው መልክ በመስጠቱ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ሁሉ የሚያኮራና የሚያስደስት ሆኖ ተገኝቷል ። የመንበረ ፓትርያርኩ ሀገረ ስብከቶችም ለዚህ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው የታወቀ ነው ፡ ከዚያም



## ዜና ሊቃውንት

# የታላቁ ሊቅ መምህር ጌጡ ተሰማ የሕይወት ታሪክ

## በአጭሩ

መምህር ጌጡ ተሰማ ከአባታቸው ከመሪጌታ ተሰማ ውቤና ከእናታቸው ከወ ሮ የተመኙ እሸቴ በ፲፱፻፲፯ ዓ ም በጎንደር ሀ ስብከት ጋይንት አውራጃ ስማዳ ወረዳ ደብረ ዕንቍ ማርያም ተወለዱ ፡ ዕድሜያቸውም ለትምህርት ሲደርስ ወላጅ አባታቸው መሪጌታ ተሰማ ውቤ የድጓ መምህር ስለነበሩ ቤታቸውን ሳይለቁ ፊደል ቆጥረው ፀዋትወ ዜማ እስከ ድጓ በሚገባ ተማሩ ።

በ፲፱፻፳፫ ዓ ም ወደ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሄደው ብቸና አውራጃ ደብረ ብርሃን ቅዱስ ጊዮርጊስ

ዝነኛ ከነበሩት መምህር ውብሸት ዕንገዳ ቅኔ ከእነ አገባቡ እስከ እርባ ትምሩ ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል ። በተጨማሪም ከእኒሁ መምህር ነገሥት የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም



መምህር ጌጡ [illegible]

ትርጉም የመዝሙረ ዳዊት ትርጓሜንና የበዓላትንና የአጽዋማትን ማውጫ የሆነውን ባሕረ ሐሳብ በሚገባ አጠናቀው ተምረዋል እንዲሁም ደብረ ድማኅ ቅዱስ ጊዮርጊስ ባሕታዊ ገብረ አብ ከተባሉ መናኝ ቅዳሴ ተምረዋል ።

በ፲፱፻፳፯ ዓ ም ወደ ትውልድ ሀገራቸው ደብረ ዕንቍ ማርያም ተመልሰው የቅኔ ትምህርታቸውን ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ ጉባኤያቸውን ሳይፈቱ እያስተማሩ በመማር ዕውቀታቸውን ለማዳ

በር ሲሉ ወደ ደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ ወደምትገኘው ማኅደረ ማርያም ሄደው ዝነኛና ታዋቂ ከነበሩት ሊቅ መምህር ክፍሌ ወልደ ጻድቅ አቋቋም ተምረዋል ።

መምህር ጌጡ ተሰማ የአቋቋም ትምህርታቸውን ተምረው ወደትውልድ ቦታቸው ከተመለሱ በኋላ ጉባኤያቸውን አስፋፍተው በንቃትና በትጋት በማስተማር ብዙ ምሁራንን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ሊቁ ማስተማር ከጀመሩ ፳፫ ዓመት እንደነበራቸው ሲታወቅ በዚህ የማስተማር ዘመናቸው አስተምረው ከማስተማር ደረጃ ያደረሷቸው ከ፩፻፶ በላይ እንደሚሆኑ ታውቋል ።

በዚህ ወቅትም መምህር ጌጡ ተሰማ ወ ሮ በላይነሽ ይታየውን በሥርዓተ ተክሊል አግብተው ፫ ወንዶችንና ፫ ሴቶች ልጆችን በድምሩ ፮ ልጆችን ወልደው ለቁም ነገር አብቅተዋል ።

መምህር ጌጡ በማስተማር ብቻ ሳይወሰኑ መልካም ተግባራቸውን ቀጥለው በመብረቅ ተቃጥላ ለብዙ ዘመን ሳትሠራ በመቆየቷ የኖረችውን የደብረ ዕንቍ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የአካባቢውን ምእመናን በማስተባበርና ከመንግሥትም ርዳታን ጠይቀው ቤተ ክርስቲያኑን በሚገባ አሳንፀው ማሪውንም በቆርቆሮ አስክድነዋል ። በዚያም የውሃ ችግር ስለነበር ፫ የውኃ ጉድጓዶችን በማ



www.ethiopianorthodox.org

ስቆሬር ችግሩ እንዲወገድ አድርገዋል ፡ በተጨማሪም የደብረ ዕንቁ የመጀመሪያው የደብሯ መምህር አስተዳዳሪ በመሆን ተሹመው ከማስተማሩ ጋር ሲያስተዳድሩ ለብዙ ዓመታት ቆይተዋል ።

መምህር ጌጡ ተሰማ ይህ ትምህርታቸው በአንድ ሀገረ ስብከት ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር በማሰብ በ፲፱፻፳፯ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጥተው መኖሪያቸውን በማኅደረ ስብሐት ልደታ ቤተ ክርስቲያን አድርገው ቅኔንና ትርጓሜ መጻሕፍትን በማስተማር ለቤተ ክርስቲያናችን ብዙ ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ሊቁ መምህር ጌጡ የተሾሙባቸውና የተሸለሙባቸው ቦታዎች

፩. ከታላቁ ደብር ድማኅ ቅ ጊዮርጊስ ካባና ቀሚስ

፪. ከቆማ ፋሲለደስ ካባና ቀሚስ

፫. ከማኅደረ ማርያም ካባና ቀሚስ

፬. ከመርጡለ ማርያም ካባና ቀሚስ

፭. ከዙር አምባ ጽርሐ አርያም ካባና ቀሚስ

፮. ከደብረ ታቦር ኢየሱስ ካባና ቀሚስ ተሸልመዋል ።

፯. በወሎ ሀ/ስብከት በአምሐራ ሳይንት ውስጥ የምትገኘው የአትሮንስ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጽሩ በዘመናዊ ሕንፃ ተሠርቶ ታቦቷ ስትገባ ከአውራጃው አስተዳዳሪ ቀሚስና ካባ ተሸልመዋል ።

፰. በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ሕቅራቢነት ወደቀድሞው ንጉሥ ቀርበው ከ፲፭ ተማሮቻቸው ጋር ተሸልመዋል ።

፱. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው በዓለ ሢመት በተከበረ ጊዜ የክብር ጥሪ ተደርጎላቸው መጥተው በአበረከቱት ቅኔ ከእነ ተማሪዎቻቸው ተሸልመዋል ።

፲. በጎንደር ሀ/ስብከት በጋይንት አውራጃ በስማዳ ወረዳ ከማስተማር ጋር የወረዳው ሊቀ ካህናት በመሆን ከ፳፭ ዓመት በላይ አገልግለዋል ።

ታላቁ ሊቅ መምህር ጌጡ ተሰማ በሚያስተምሩት ትምህርትና በሚፈጽሙት መንፈሳዊ አገልግሎት በቃኝ ብለው ሳይገቱ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በኩል በማኅሌትና በስብከተ ወንጌል ሌት ከቀን ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ኑረዋል ።

ያለ ድካምና መሰልቸት በሚሰጡት ቅን አገልግሎት በኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ዘንድ በመታወቃቸው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ጎብኝተው ተመልሰዋል ። እኚህ ሊቅ አባታዊ ምክራቸውን ለማንም ከማካፈል የማይቆጠቡ ድሃ ሀብታም ትንሽ ትልቅ በማለት ሰውን ለማበላለጥ የማይፈልጉ ከመልካም ነገር በስተቀር በክፉ ተግባር የማይሠማሩ ሰውን አክባሪ እግዚአብሔርን ፈሪ ለሰው ሁሉ አዛኝና ሩኅሩኅ እንደነበሩ ዝናቸው የታወቀ ነው ።

ነገር ግን ሥጋ የለበሰ ሁሉ አዳም ሆይ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ ከሚለው አምላካዊ ቃል ለማምለጥ ስለማይችል እኚህ የቤተ ክርስቲያናችን ማኅቶት የነበሩት ታላቅ አባት ከመካከላችን በኃያሉ አምላካችን ፈቃድ በሞት ሲለዩን መሪር የሆነ ኀዘን ቢሰማንም ትተውልን በሄዱት መልካም ሥራቸው እንጽናናለን መምህር ጌጡ ተሰማ ከቅርብ ቀን ወዲህ ባደረባቸው ሕመም

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## ሠ/ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከሀገሯ ውጭ ክርስትናን ለማስፋፋት ያደረገችው (የፈጸመችው) የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ።

ከሙ ሉሌ መልአኩ

ከታሪክ እንደምንመለከተው ክርስትና በጌታና በሐዋርያት ከተሰበከችበት ጊዜ ጀምሮ የወንጌል መልእክተኞች (ሐዋርያት) በመላ ዓለም በአደረጉትና አሁንም በሚያደርጉት ስብከት እየተስፋፋች የመጣች ሃይማኖት ናት ።

በወንጌላዊው ማርቆስ ስብከት ክርስትናን የተቀበሉ አባቶችም ወዲያው በተራቸው (በበኩላቸው) የወንጌል መልእክተኞችን በመላክ ከግብጽ ውጭ ከሚኖ

ምክንያት ሰኔ ፯ ቀን ፲፱፻፲፩ ዓ ም በተወለዱ በ፸፯ ዓመታቸው ማስተማር በጀመሩ በ፶፫ ዓመት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩንም በረድኤት እንደማይለዩን እናምናለን።

ስለዚህ ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን ለወገኖቻቸው መረጋጋትን እንዲሰጥልንና ነፍሳቸውን በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ ቃል ኪዳን በምትወረስ በመንግሥተ ሰማያት እንዲያስቀምጥልን አምላካችንን እንለምናለን ።

የዜናው አቅራቢ ሊ/ኅ /ልሣነ ወርቅ በዛብኅ



ረው ከሌላው ሀገር ሕዝብ ጥቂቱን በትጋት አስተምረው ወደ ክርስቶስ መልሰዋል ።

በሜዲትራንያን (በታላቁ) ባሕር ዳር የምትገኘው እስክንድርያ የጥንታዊው ዓለም ሕዝብ ማለት የአሕዛብና የአይሁድ መናሃሪያና መተላለፊያ የንግድ ማዕከል ስለነበረች የተለያዩ ሀገር ነጋዴዎች የጐበኟት ነበር ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከፍተኛ መንፈሳዊና ዓለማዊ ትምህርት ለመቅሰም ከተለያዩ ሀገሮች የሄዱ ደቀመዛሙርትም እስክንድርያ ውስጥ በነበረችው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተምረዋል ።

እላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ሕዝብ ጋር ግንኙነት በማድረግ የወንጌል መልእክተኞቿን ወደተለያዩ ሀገሮች በመላክ ክርስትናን አስተምራለች ።

ክርስትናን ከሰበከችባቸውም ሀገሮች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

፩ ቀሬና (ሊቢያ) ። በሐዋርያት ሥራ ፪.፲ የቀሬና ተወላጆች የነበሩ አይሁድ የፋሲካን በዓል ለማክበር በመሄዳቸው በጰንጠቆስጤ ዕለት ጴጥሮስ ሲያስተምር ኢየሩሳሌም እንደነበሩ ተገልጿል። ሆኖም የክርስትና ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ የሮም ቅኝ ግዛት በነበረችው ቀሬና ውስጥ በይፋ የተሰበከችው በቅዱስ ማርቆስና በረዳቶቹ ግብፃውያን የወንጌል መልእክተኞች መሆኑ ይነገራል ።

የቀሬናው ተወላጅ ሲኔሲዮስም (፫፻፸—፬፻፲፬) በእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በእስክንድርያ ፓትርያርክ በቴዎፍሎስ በ፬፻፲ ዓ/ም የቀሬና ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ በመሾም በሀገሩ ክርስትናን አስፋፍቷል ።

በ፫፻፳፭ ዓ/ም (፫፻፲፯ ኢ.ዘ.ፍ አቆጣጠር) በተደረገችው በመጀመሪያዋ የኒቅያ ጉባኤ ለመካፈል የተሰበሰቡት አባቶችም የቀሬና (የፔንጳፖሊስ) ሀገረ ስብከት በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሥር እንዲሆን ወስነዋል ። ከዚህም ውሳኔ የምንገነዘበው ከሰሜን አፍሪካ ቀሬና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ስብከት ክርስትናን ስትቀበል ፡ ካርቴጅ ግን ክርስትናን የተቀበለችው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስብከት መሆኑን ነው ።

፪/ኖብያ (ደቡብ ሱዳን) ። የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በኖብያ የክርስትናን ትምህርት በማስተማር ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ መልሳለች ። ከወንጌል መልእክተኞች ከፈሎቹ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ላይ በየጊዜው ከተነሡት ስደቶች እየሸሹ ኖብያ የገቡ ኮፕቶች እንደነበሩ ይተረካል ። በአባ እንጦንስ የተመሠረተውም የብሕትውና ኑሮ በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኖብያ ተዛምቶ ስለደረሰ ገዳማት ተመሥርተው ነበር ።

የቢዛንታይን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም (፫፻፳፯ ፫፻፷፭) በሥሩ በሚተዳደሩ የቅኝ ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ክርስትናን እንዲቀበሉ ያወጀው ትእዛዝ ኖብያም ውስጥ ከአሕዛብ ወገን ብዙዎቹ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረውን የክርስትና እምነት እንዲቀበሉ ረድቷል ። በኬልቄዶን ጉባኤ ከተደረገው መለያየት በኋላ በቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያንና በንጉሡ የሚደገፉት የሁለት ባሕርይን እምነት ተቀብለው እስክንድርያ የሚኖሩት መለካውያን (የቢዛንታይን ንጉሥ ታማኝ ደጋፊዎች) የተባሉት ክርስቲያኖች በኮፕት ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ተጽእኖ ያደርጉ ነበር ። ሆኖም የአንድ ባሕርይን (የተዋሕዶን) እምነት ተከታዮች በኅቡዕ ትደግፍ በነበረችው በእቴጌ (በንግሥት) ቴዎዶራ እርዳታና ድጋፍ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በኖብያ ለሚኖሩ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ክርስቲያኖች በ፭፻፵፱ ዓ/ም ለዋናዋ ከተማ ለናፓታ ሎንጊኑስ ለተባለው ካህን የጵጵስና ማዕርግ በመስጠት ሾማለች ። ሎንጊኑስም ረዳቶቹ ከሆኑ ካህናት ጋር ኖብያ ውስጥ ክርስትናን በትጋት አስተምሯል ። ቀስ በቀስም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ታነጹ፡ ገዳማትም ተመሠረቱ ፡ ከነሱም አንዱ ታላቁ የቅዱስ ስምዖን ገዳም ነበር ። በዚህ አኳኋን የኖብያ ሕዝብ ክርስትናን ተቀብሎ ሲኖር ግብጽን ከወረሯት እስላሞች ጋር እየተዋጋ ነጻነቱንና እምነቱን ጠብቆ ከቆየ በኋላ ሰላዲን በላከው የግብጽ ጦር በአሥራ ሦስተኛው መቶ ዘመን ሰሜናዊው የሀገሩ ክፍል በእስላሞች እጅ ወደቀ ። የቀረው ክፍለ ሀገር ሕዝብ ግን በጀግንነት ሲከላከል ከቆየ በኋላ በአሥራ ስምንተኛው መቶ ዘመን በመሸነፋቸው የፖለቲካና የሃይማኖት ነፃነታቸውን ተገፈፉ ። ሆኖም ክርስትና ከምድረ ኖብያ ለጊዜው የጠፋች ብትመስልም እንድያውን አልተደመሰሰችም ። ለዚህም ማስረጃ በዘመናችን ኮፕቶችና ሌሎችም የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በሱዳን (በደቡብ ሱዳን) ውስጥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን መሥርተው ወንጌልን በስ



www.ethiopianorthodox.org

ሩት በመስበክ ላይ ናቸው ።

፫ ኢትዮጵያ ፡ ከታሪክ እንደ ምንመለከተው ዋና መናገሻ ከተ ማው አክሱም የነበረው የኢትዮ ጵያ ሕዝብ ከክርስቶስ ልደት በፊት በክፈል የአይሁድን እም ነት ተቀብሎ ሲኖር ፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፴፬ ዓ ም ደግሞ ከፈልጶስ በተማረው የሕንደኬ በጅሮንድ አማካይነት የክርስት ናን ዜና ሰምቷል (የሐ.፰.፳፯

፴) ፡ ሆኖም እስከ ፫፻፴ ዓ ም ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአሪት እምነቱ ጋር ተምቀትን ተቀብሎ ከቆየ በኋላ የክርስትና እምነት በይፋና በሰፊት ሊሰበክ የተቻ ለው በ፫፻፴ ዓ ም የእስክንድር ያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴ ዎስ ለፍሬምናጦስ (ለሰላማ ፡ ለከ ሣቴ ብርሃን) ማዕርገ ጵጵስና ሰጥቶ ወደ ኢትዮጵያ ከላከው በኋላ ነው ፡ በስብከትና አብያተ ክርስቲያናትን በመመሥረት የሚ ረዱትን ንብረትያንን ካህናትም ከአባ ሰላማ ጋር አብሮ እንደላከ ይታመናል ፡ ምንም እንኳ የኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተ ኞቹን ልካ በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ባትካፈልም በቅዱስ ዲዮስቆሮስ የተወከሉትው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበለውን ተተተ ኛውን የተዋሕዶ እምነት ተቀብላ በተግባር ላይ አውላለች ።

፬ እስያ ፡ የእስክንድርያ ፓትር ርያርክ ቀዳማዊ ዲሜጥሮስ የእስክ ንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መሪና አስተማሪ የነበረውን ፓን ጤኖስ የተባለውን ምሁር በ፩፻፹ ዓ ም ወደ ሕንድ በወንጌል መልእ ክተኛነት ስለላከው ተደም ሲል በሐዋርያው ቶማስ የተጀመረውን የክርስትና ትምህርት ሕንድ ውስጥ አስተምሯል ፡ ኢሱም የተ ላከበትን የሐዋርያነት ተግባር ፈጽሞ ሲመለስ አገሬመንንናን በረቢ ያ ሬሊክስ (የመን) አርር ክርስትናን መስበኩ ይነገራል ፡

በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ወደ ሕንድ የተጓዘው ኮስማስ ኢን ዲኮፕሌውስቱስ የተባለው እስክ ንድርያዊ የጅኦግራፊ ምሁርና ነጋዴ ወደ ሕንድ በመርከብ በተጓ ዘበት ወቅት በፋርስ ባሕረ ሰላጤ፡ በሳኮትራ ደሴቶች ብዙ ክርስቲያ ናችንና ምእመናን የሚያገለግሉ የሚመሩ) ጳጳሳት ማየቱን ገል ጿል ፡ ሕንድም ውስጥ በሐዋር ያው ቶማስ የተመሠረቱትው ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑ ብዙ ክር ስቲያናችን ማየቱን ገልጿል ፡

፭ አውሮጳ ፡ ምንም እንኳ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መልእክተኞቿን በተ ቀጥታ ልካ አውሮጳ ውስጥ ባትሰብ ክርም ቅሉ የእስክንድርያው ፓት ርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ በሀ ለ ተኛው የስደቱ ወቅት ወደ ሮም ተሰዶ ከ፫፻፵፱ እስከ ፫፻፵፯ ዓ ም ድረስ ከሮም ፓፓ ተዳማዊ ጁል ዩስ ዘንድ በእንግድነት በቆየበት ወቅት በእነ አባ እንጦንስ እምነ ዮስ ፡ መቃርስ፡ ጳኩሚስ ወዘተ ገብጽ ውስጥ የተመሠረተውን የብሕትውና ኑሮን ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አባላት አስ ረድቷል ፡ በዚሁም ትምህርት መሠረት በአውሮጳ የብሕትውና ኑር በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሊስፋፋ ፖር ሊሰድ ቻለ ፡ ከአውሮጳ ወደ ገብጽ ሄደው የብሕትውናን ኑር ካጠኑና ከተለማመዱ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ስለ ብሕት ውና ኑርና ሕግ ከጻፉትና የብሕት ውናን ኑር ከመሠረቱት እንዱ ጆን ካሲያን (፫፻፷ ፬፻፴፭) የተባ

# ቅ... ሩፋኤል ለጦብያ

(ካገጽ ፲፬ የዞረ)

ኔን ታውቁ ዘንድ ኛላችሁን እኔ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ የሆንኩኝ ሩፋኤል ነኝ ብሎ ሲገልጽላቸው ሬሩ እጅግም ደነገጡ ቅዱስ ሩፋ ኤል ግን ጦብያን ከዓማ እፍ ያዳን ኩት በግራ ወለተራጉኤል አድሮ የነበረውን አስማንድዮስ የተባለ ውን መንፈስ ርኩስ ያባረርኩት ያንተንም ዓይን ያዳንኩ እኔ ሩፋ ኤል መሆኔን ዕወቁ ሲል ራሱን በራሱ ካስተዋወቀ በኋላ ለወደፊ ትም በረድኤት እንደማይለያቸው ተስፋ ሰጥቷቸው አማላጅነቱንም አስወቃቸው ከፊታቸው ተሠ ወረ።

እነርሱም እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በእግዚአብሔር በምሥጋናዊ ትን እየመሰከሩ የቅዱስ ሩፋኤል ንም አማላጅነት እያስታወሱ ኑረው አልፈዋል ።

ለጦቢትና ለጦብያ ይህንን ዕድል ሊያጋጥማቸውና ከመል አኩ ቅዱስ ሩፋኤልም አማላጅ ነት ሊሳተፉ ያስቻላቸው ሃይማኖ ታቸውና ምጽዋታቸው በጠቅላላ መንፈሳዊ ምግባራቸው መሆኑን ተገንዝበን እኛም ከዚህ እንዲህ ካለው ጸጋ ተሳታፊዎች ሁነን እን ድንገኝ በሃይማኖታችን ጸንተን መኖር ይፈለግብናል ።

ከነፈ ርግብ ግርቁስ

---

ለው መነኩሴ ነበር ፡ እሱም ይህ ንኑ የብሕትና ኑር የመሠረተ በት ውልድ ሀገሩ ፈረንሳይ ውስጥ ግር ሴይ አካባቢ ነበር ፡



# የማኅበረ ሥላሴ ገዳም ታሪክ በአጭሩ


የማኅበረ ሥላሴ ገዳም የሚገ ኘው በጎንደር ሀ/ስብከት በጭልጋ አውራጃ ነው ቦታው በረሃ በመ ሆኑ የወባ በሽታ እጅግ በጣም ይበዛበታል ከፀሐይ ብርታት የተ ነሣ በደንጊያ ላይ ተልባ ያስቆላል እየተባለ ይነገራል ።

ከዚህ ቆላ መካከልም አራት አንባዎች ይገኛሉ እነርሱም ከር መች ኩክቢ ጉርማስ ድባ የሚ ባሉ ሲሆኑ አራተኛው አንባ የማ ኅበረ ሥላሴ ገዳም የሚገኝበት ነው ገዳሙ የአንድነት ነው ከተ መሠረተ ጀምሮ ሥርዓቱ እስከ ዛሬ ድረስ ሳይለወጥ ጸንቶ ይገ ኛል።

ገዳሙን የሸፈኑት ሰርኪን ሲና፡ ዋሊያ መቀር ዋርካ ሽመልና የመ ሳሰሉም ዕፀዋት ናቸው ፡ የዱር አራዊትም በየዓይነታቸው በብ ዛት ይገኛሉ ። በዚህ ሜካና ይን ገዳም የክብት ግጦሽ እንደልብ ስለሚገኝ የገዳሙ መነኮሳት የሚ ረዱት የቀንድና የጋማ ከብቶችን በማርባትና በእርሻና በቁፋሮ ነው።

ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ የጉ ድጓድ ውሀ ብቻ ይገኛል ትንሽ ዝቅ ብሎ ደግሞ ከሦስት ላይ የምንጭ ውሀ ይገኛል ከዚህ በተ ረፈ ከገዳሙ ራቅ ብሎ ከሚገኘው ወንዝ በሸራ እየተቀዳ በበቅሎና በአህያ ላይ እየተጫነ ወደ ገዳሙ በመግባት ለመነኮሳቱ አገልግ ሎት ይውላል እንግዳ ሲመጣ የገ ዳሙ መነኮሳት ተቀብለው እግር አጥበው መቁነን ሰጥተው እስከ ሰባት ቀን ያስተናግዳሉ ።

የመነኮሳቱ ምግብ ጤፍና ማሽላ ዳጉሳ ዱቄት በአንድነት



ተቦክቶ በአንባበር መልክ ተጋ ግሮ በቢላዋ (በሰንጢ) ከሦስት ከሦስት እየሆነ ይቆረስና በ፲ ሰዓት ላይ በደወል መነኮሳቱ ተሰ ብስበው በአንድነት ጸሎተ ማዕድ ጸልየው መቁንናቸውን እየተቀ በሉ ወደየቤታቸው ይሄዳሉ ምግ ባቸውም መኮሬታ ይባላል ይህንን

www.ethiopianorthodox.org

ምግባቸውን የሚበሉበት በፋጋ ወጥ ይሰጣቸዋል ። የሚጠጡትም የኑግ ውሃ እየተለካ ይሰጣቸዋል ።

እሁድና ቅዳሜ በሦስት ሰዓት ላይ ምግባቸው ይሰጣቸዋል እንጂ እንደሌሎቹ ቀናት እስከ ፲ ሰዓት አይውሉም ከውጭ የበሰለ ምግብ ወደገዳሙ ፈጽሞ አይገባም እንዲሁም ጫማ በእግር ተጫምቶ የጦር መሣሪያ ይዞ ወደ ገዳሙ መግባት ክልክል ነው ። የግዝት በር የሚባል አለ ሴቶች ያንን በር አልፈው መግባት አይፈቀድላቸውም በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሳት ከምሳቸው ወይም ከራታቸው ቀን ሰው ጧት ቁርስ መመገብ አይፈቀድላቸውም ከመነኮሳቱ መካከል የግሉ የሆነ መርፌ ምላጭ ትርፍ ልብስና ከፍተኛ መጽሐፍ ከአንድ ሳንቲም ጀምሮ ጥሬ ብርና ሳንቲም በመኖሪያ ቤት ማዋል ማሳደር አይቻልም ።

ራሱን ለመላጨት ጥፍሩን ለመቁረጥ ፡ ልብሱን ለመስፋት ከመጋቢው አስፈቅዶ በትውስት ከዕቃ ቤቱ ሊወስድ ይችላል ። ከመነኮሳቱ መካከል ማንኛውም ቢሆን በግል ፈቃዱ እንደልቡ የግል ጥሪት ቁሪት ሊያከማችና እንደፈለገ ይሆን ዘንድ አይፈቀድለትም ምግብ ግን ከፈለገ ግማሽ መኮሬታ በተወሰነው ሰዓት ይፈቀድለታል ፡ ውሀም እንደምግባቸው በተወሰነ የውሀ መያዣ በትክክል ይቆነናሉ እንጂ እንደፈለጉ ውሀ ነው ብለው መጠቀም አይችሉም ። ልብሳቸውም ሆነ ምግባቸው አንድ ዓይነትና ትክክል ነው።

ገዳሙን በሥርዓት አበው የሚያስተዳድሩ ፯ አበው መነኮሳት አሉ እነርሱም ፡

፩ኛ. መምህር (አበምኔት)
፪ኛ. መጋቢ
፫ኛ. ሊቀ ረድዕ
፬ኛ. አጣኝ
፭ኛ. ዕቃ ቤት
፮ኛ. ሊቀ አበው
፯ኛ. ዕጓል መጋቢ ናቸው ።

ቀደም ባለው ዘመን አፈ መምህር የሚባል የውጪውን ጉዳይ ፈጻሚ ነበር ። አሁን ግን ሁሉም በመምህሩ በአበ ምኔቱ ተጠቃሎ ይሠራል የዚህንን ገዳም ሥርዓት የወሰኑት ጻድቁ አባ ዓምደ ሥላሴ ናቸው ።

ገዳሙ የተመሠረተው በዓብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት በ፬ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ነው አብርሃ ወአጽብሐ የተባሉት የኢትዮጵያ ነገሥታት ጳጳሱ አባ ሰላማ (ፍሬ ምናጦስ) በዚሁ ገዳም ፫ ቀን ውለው አድረው ቦታውን በሚገባ ተመልክተውታል ። ከዚያም ሳሉ ፍሬምናጦስ ሌሊት ቁሞ ሲጸልዩ የብርሃን ልብስ የለበሱ ሦስት ሰዎችን አየ ያየውንም ለአብርሃ ወአጽብሐ ነግሮ ከዚህ ቦታ በሥላሴ ስም ቤተ ክርስቲያን ቢታነፅ መልካም ነው ብሎ ነገራቸው እነርሱም በአሳቡ ተስማሙለት ወዲያው ቤተ ክርስቲያኑ ተጀመረና ሲፈጸም ታቦተ ሥላሴ ገብቶ ቅዳሴ ቤቱ ከተከበረ በኋላ አብርሃ ወአጽብሐ ይህ ቦታ ዱሩ እሳት መካከሉ ገነት ይሁን የበረረ ወፍ የሠገረ ቆቅ አይታደንበትም ከገዳሙ አበ ምኔት በስተቀር ሥጋዊ ዓለማዊ ዳኛ እንዳያዝበት ብለው ወስነዋል ።

ጳጳሱ አቡነ ሰላማም የነገሥታቱን ቃል በጽሑፍ አስፍረው ሕጉን ሥርዓቱ የጸና ሆኖ እንዲኖር በሥልጣናቸው አውግዘው ፡ የቦታውም ስም ምቋመ ሥላሴ ተብሎ እንዲጠራ አደረጉ ።

በ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል እንዲሁም የቅዱሳን አጽም ከኢየሩሳሌም ወደ ሀገራችን ሲመጣ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም ሶስት ቀን ውሎ አድሯል ። በዚያን ጊዜም ብርሃን እንደአንፀባረቀበት ይነገራል ።

ከዚያ ወዲህ የብዙ መናንያን መኖሪያ በመሆን የአንድነት ገዳም ሆኖ ኑሯል በገዳሙ የበቁና ለብዙ ዘመን የዘጉ መናንያን ስለሚኖሩበት ገዳሙ ዝነኛ ሆነ ።

ሱስንዮስ የተባሉ ንጉሥ ተነሥተው ከጥንት ተያይዞ የመጣውን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን ትተው የካቶሊክ እምነትን ተቀብለው ሕዝቡም እንዲቀበል ዓዋጅ አስነገሩ ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብም የአባቶቻችን እምነት ትተን የካቶሊክ ሃይማኖትን አንቀበልም በማለት ዓፄ ሱስንዮስን እየወገዘ የሚገደለው ተገደለ የሚሰደደው ወደጐረቤት ሀገር ተሰደደ አባ ዓምደ ሥላሴም የተባሉ ኢትዮጵያዊ ወደ ግብፅ ተሰደው በገዳመ አስቄጥስ እየረዱ ተቀመጡ ።

ከዚህ በኋላ ዓፄ ሱስንዮስ በጸና ታመሙ ምላሳቸውም ወጥቶ እንደውሻ እያለከለኩ ይጨነቁ ጀመር አባ ዓምደ ሥላሴም ወሬ ሰምተው ኢትዮጵያ ሀገሬ ሰላም ካገኘች ወደ ሀገሬ ልመለስ ብለው መጡና በማኅበረ ሥላሴ ገዳም ተቀመጡ የዓፄ ሱስንዮስ ልጅ አቤቶ ፋሲል አባታቸውን ከሕማማቸው በጸሎቱ ኃይል የሚያድንላቸው መነኩሴ ካህን ወዴት እንደሚገኝ ቢያጠያይቁ አባ ዓምደ ሥላሴ በማኅበረ ሥላሴ መኖራቸው ለአቤቶ ፋሲል ተነገራቸውና መልእክተኛ ላኩ አባ ዓምደ ሥላሴ የአቤቶ ፋሲል መልእክት



እንደደረሳቸው የሮም ሃይማኖት ወደሀገሩ እንዲሄድ ፡ የእስክንድርያ ሃይማኖት እንዲመለስ የሚደረግ ከሆነ በእግዚአብሔር ቸርነት እኔ የታመሙትን ዓፄ ሱስንዮስ አድናቸዋለሁ ብለው መልሰው ላኩ አቤቶ ፋሲልም መልእክቱ እንደደረሳቸው ደስ ብሏቸው አባቴ ሆይ ያሉት ይደረጋል ይምጡልኝ ብለው ላኩባቸው አባ ዓምደ ሥላሴም ደጋግ መነኮሳትን አስከትለው ሂደው ደንቀዝ ቤተ መንግሥት እንደደረሱ አቤቶ ፋሲል በክብር ተቀበሏቸው ።

በመልእክት የተነጋገሩትን በቃል አጽድቀው ከአስከተሏቸው መነኮሳት ጋር ሶስት ሱባዔ ሲጸልዩ ሰንብተው በጸበል በመጥመቅ አድነው በማስተማር የክርስቶስን ሥጋና ደም ሲያቀብሏቸው ተጐልጉሎ ወጥቶ የነበረው ምላሳቸው ወደጥንት ቦታው ተመለሰላቸው አእምሯቸውንም አውቀው ከተኙበት አልጋ ብድግ ብለው ተነሥተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ ።

አባ ዓምደ ሥላሴም ንጉሥ ሆይ የእግዚአብሔርን ተአምራት ካየህ የእስክንድርያ ሃይማኖት ትመለስ የሮም ሃይማኖት ይሠረዝ ሱስንዮስ ከመንግሥቱ ይፍለስ ፋሲል ይንገሥ ብለህ ዓዋጅ አስነግር አሏቸው ሱስንዮስም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ይመለስ የካቶሊክ ሃይማኖት ይፍለስ ፡ ፋሲል ይንገሥ ብለው ዓዋጅ አስነገሩ ። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ከፍ ያለ ደስታ አደረገ ፡ አቤቶ ፋሲልም በአባ ዓምደ ሥላሴ አንጋሽነት ዓፄ ፋሲል ተብለው ነገሡ በአባታቸው ዙፋንም ተቀምጠው ሕዝቡን በትክክል ማስተዳደር ጀመሩ።

የእስክንድርያ ሃይማኖት ተመልሳ ተቋቋመች የሮም ሃይማኖት መሪዎች ሃይማኖታቸውን ይዘው ወደ ሀገራቸው እንዲባረሩ ተደረገ ዓፄ ፋሲልም አባ ዓምደ ሥላሴን በፍቅርና በሰላም አነጋግረው ለአባቴ ያደረጉልኝን ውለታ እኔም መመለስ ስለአለብኝ ምን ላድርግልዎ አሏቸው አባ ዓምደ ሥላሴም ንጉሥ ሆይ በጭልጋ አውራጃ ውስጥ ጥንት አብርሃ ወአጽብሐ አባ ሰላማ የተከሉት የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አለ የስሙም መጠሪያ ምቋመ ሥላሴ ነው ። በዚህ ገዳም ብዙ መናንያን መነኮሳት ስለሚኖሩበት ለገዳሙ መርጃ የሚሆን ሰፊ የእርሻ መሬት እንዲሰጡኝ ነው የምጠይቀው አሏቸው ዓፄ ፋሲልም ለገዳሙ መናንያን እራሽ የሚሆን ጣቁሳ ከሚባለው ቦታ ላይ ፺፬ ጉልት መሬት ሰጥቼዎታለሁ ። ይህንንም የሚያርሱበት አምሳ ጥንድ በሬዎች አንድ መቶ ጭነት እህል በየዓይነቱ እንዲሰጥዎ ፈቅጃለሁ ፡ የገዳሙም ስም ማኅበረ ሥላሴ ተብሎ ይጠራልዎት ብለው ወሰኑላቸው አባ ዓምደ ሥላሴም ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ንጉሥ ሆይ ዘመንዎ ዘመነ ሰላም ይሁንልዎ እግዚአብሔር መንግሥትዎን ይባርክልዎ ብለው መርቀውና ባርከው የተሰጣቸውን ስጦታ በመመዝገብ ገዳማቸውን በደንብ አቋቁመው አበው መነኮሳትን አሰባስበው የአንድነት የንፍሮ የመኮሬታ ምግብ የተወሰነለት ገዳም አድርገው ሥርዓተ አበው የሚባል መጽሐፍ ጽፈዋል ፡ በመጨረሻም እኒህ መነኩሴ ብዙ አስደናቂዎች የሆኑ ትሩፋትና ተአምራት ሠርተው በአንድ መቶ አራት ዕድሜያቸው የካቲት ፳፯ ቀን አርፈው በማኅበረ ሥላሴ ገዳማቸው ተቀብረዋል በመቃብራቸውም ላይ ልዩ ልዩ ተአምራት ይሠራበታል ።

## ዜና ዕረፍት

### መምህር ጌጡ ተሰማ በተወለዱ በ፸፮ ማስተማር በጀመሩ በ፶፫ ዓመታቸው አረፉ

ታላቁና ዝነኛው ሊቅ መምህር ጌጡ ተሰማ ከቅርብ ቀን ወዲህ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ሰኔ ፯ ቀን ፲፱፻፸፭ ዓ ም ከቀኑ በ፱ ሰዓት አዲስ አበባ ከተማ በስተደቡብ በምትገኘው ማኅደረ ስብሐት ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

ዜና ሞታቸውም እንደተሰማ የደብሩ ካህናትና በአካባቢው የሚኖሩ ምእመናን አስከሬናቸውን ወደ አለበት መጥተው ኀዘናቸውን ከገለጹ በኋላ አስከሬኑ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተወስዶ ጸሎተ ፍትሐት ሲደረግለት አደረ ።

በበነጋው ሰኔ ፰ ቀን ፸፭ ዓ ም የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ካህናት አስከሬናቸው ወደሚገኝበት ማኅደረ ስብሐት ቤተ ክርስቲያን መጥተው ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ በአንድ ወገን ሊቃውንቱና መዘምራኑ በሌላ ወገን በመሆን

የዜናው አቅራቢ
አባ ገ/መስቀል ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም

ይቀጥላል



www.ethiopianorthodox.org

ጸሎተ ፍትሐት ሲያደርሱ ውለ ዋል ፡፡ ሊቃውንቱ ስብሐተ ነግህ ቆመው ከመዋላቸውም ጋር በሰ ዓቱ የፍትሐት ጉዞዎች ሁሉ አቡን እየቃኙ እየዘመሙ መዋሥ ዕት እየመሩ ለዘብ እያለዘቡ እጅግ በጣም በሚያስገርምና በሚያስደ ንቅ ሁኔታ ሲፈቱ መዋላቸው ታውቋል ፡፡

በዚሁ ዕለት ስለሊቁ መምህር ጌጡ ተሰማ ቁጥራቸው በርከት ያለ ምሥጢራቸውም ጠለቅና ረቀቅ ያለ ቅኔዎች ተደርሰዋል ፡፡ በዕለቱ ከደረሱትም ቅኔዎች ጥቂ ቶቹን ቀጥለን አቅርበናቸዋል ፡፡

፩ኛ. ዘአምሳኪየ ቅኔ ከመ ሐ ዲስ ልሣኑ ማኅደረ ስብሐት ልደታ ተበሃሉ ሕዝብ ወግ ብረ ትሕትና ክልኤቱ ፡ ዓይ ቲኑ መ ማኅደረ ዚአነ ዘንበ ውዕ ቦቱ ፡ እስመ ተክለ መድኅን ቤትነ እኅዱ ምግ ቡረ ዕደ ሞት ውእቱ፡፡

ትርጓሜው

ሕዝቦችና የትሕትና ሥራ ሁለቱ የምናድርበት ቤታ ችን ወደፊት ነው አሉ ፡፡ ቤታችን ተክለ መድኅን (መምህር ጌጡ) በሞት እጅ ፈርሶብናል እና ፡፡

፪ኛ. ዘአምሳኪየ ቅኔ ክርእሰ ደብር ትርጊት ቂርቆስ

ሞተ ፍጡራን ኃያል ለእመ ገብረ ጼዋዌ

ተሠርገወ እስከ ፍጻሜሁ ዘዓ ለም ሥርጋዌ

እስመ ኢያዕረፈ ዘልፈ ወዘ ኢረሰአ ህላዌ

ትርጓሜው

ኃይለኛ የሆነ የፍጡራን ሞት ምርኮን ባደረገ ጊዜ ከግር እስከ ራሱ ሽልማትን (መምህር ጌጡን) ተሸለመ ፡፡ ዘወትር ከመ ግደልና ከማሸነፍ አያርፍምና፡፡

ሥላሴ ቅኔ መልእክ ስብሐት ተሰፋ መርሻ ቂርቆስ

ድጓረ ረእየ በዓይነ ሥጋ ሥር ጋዌ ደብረ ዕንቍ እግዚአ ኩሉ እምሕማማቲሁ ለኢዮብ ሕዝበ እስራኤል ቀደምት ተሠይመ በላኤ መጽሐፍ ሕዝቅኤል መቅበርተ ወዘእንተ ወላዲ መካነ ይዕዜ ከመ ካልዓት አን ስት

ማኅደረ ስብሐት ተሰምየት እምሐዳስ ኀድቅ ውሉደ መዓ ልት

ካህናተ ኃጢአ በሞት

ትርጓሜው

ሕዝቅኤል መቃብር የሁሉን ጌታ የደብረ ዕንቍን ሽልማት (መምህር ጌጡን) በዓይነ ሥጋ ካየ በኋላ የመጽሐፍ ቀበኛ ተብሎ ተጠራ ፡፡

ማኅደረ ስብሐትም ዛሬ እንደሴ ሎች መካኖች ሴቶች መካን ተብላ ተጠራች ካህናትን (መ ጌጡን) በሞት አጥታለችና ፡፡

ዘይዕዜ ቅኔ መሪጌታ አፈወርቅ ቂርቆስ

የሐውር ዘር ኀበ ገራህቱ ኀበ ዘርዕኒ ኢሐረ ገራህተ አብርሃም ኀበ

ዘተከፈልዎ ብዙኃን ፡ ይባዕነበ ደብረ ዕንቍ አቡነ መምህር

ወታስቆቁ ደመ ደብረ ዕንቍ ዘኢያዜር

እንዘ መጽሐፈ ላህ ትጽሕፍ ወታለ መሪር

ጥበባትሂ ተቀብሩ እምዘኢሳይ ያስ ምድር

ትርጓሜው

ዘር ወደ እርሻው ይሄዳል ፡ የደጉ የአብርሃም እርሻም ወደዘር አልሄደም ብዙ ሰዎች የተካፈሉት አባታችን መምህር ጌጡ ወደ ደብረ ዕንቍ ይገባ ዘንድ ኢያዜር ደብረ ዕንቍ ደም ታለቅሳለች የልቅሶ መጽሐፍንና መራራ ቃልን እየጻፈች ጥበቦችም ከኢሳ ይያስ ምድር ውስጥ ተቀበሩ ማለት ነው፡፡ ጸሎተ ፍትሐቱ ሲከ ናወን ውሎ ወደ ፍጻሜ ሲቃረብ ለአሥር ሰዓት ሩብ ጉዳይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትር ያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮ ጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን ማኅደረ ስብሐት ልደታ እንደደረሱ አስከሬኑ ልብሰ ተክ ህኖ በለበሱ ቀሳውስት ግራና ቀኝ ታጅቦ ሊቁ በየጊዜው የተሸለሚ ቸው የክብር ልብሶችና ዕቃዎች በዲያቆናት ተይዘው በአስከሬኑ ፊት ለፊት ሲያመሩ በዚያ የሚ ገኙ የሰንበት ተማሪችም የኀዘን መዝሙር እያሰሙ እንባቸውን ያፈሱ ነበር ፡ በብዙ ሺህ የሚቆ ጠሩ ምእመናንም በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ሆነው ኀዘናቸውን በልዩ ልዩ ሁኔታ እገለጹ ወደ መካነ መቃብሩ አምርተዋል ፡፡

አስከሬኑ ወደ ከርሠ ምድር በሚወርድበትም ጊዜ ቀስተ ደመና መጥቶ ማታ ማታ ቆመው ጸሎት ያደርሱበት ከነበረውና ከመቃብሩ ላይ ስለተተከለ በዚያ የነበረው አዘንተኛ መንፈሳዊ ደስ ታውን በልልታና በጭብጨባ ገል ጿል ፡፡

ከዚያም በኋላ የሊቁ መምህር ጌጡ የሕይወት ታሪክ ተነቦ ሲያ በቃ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ምዕራገ ጸሎት አድርገው ሲያበቁ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መር ቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን ወደ መንበረ ፓትረክናቸው ሲመለሱ ኀዘንተኛው የሚቼን ቢተሰቦች እየተሰናበተ ወደየቤቱ ተመል ሷል ፡፡

ስለ መምህር ጌጡ ተሰማ ሞት የተደረሰ አማርኛ ድርሰት

፩. መሬት አደራሽን ያዥው ተጠ ንቅቀሽ፡
የሰጠንሽ ጥላ ጌጡ እንዳይበ ላሽ፡፡

፪. ሴቶችም ወንዶችም ገበያ ወጥ ታችሁ ፡ መስታወት ምረጡ ፡
መስታወት ነውና የሰው ሁሉ ጌጡ፡፡

፫. ሊቃውንቱ ሁሉ እስኪ ተሰብ ስቡ ሞትን እንውቀሰው፡
አሁን ምንአለበት ሥርጋዌን ቢረሳው፡
ምንም አይጎዳ ቢቀርም አንድ ሰው ፡፡

፬. ጭቃ ቀለም ግዛ የልደታ መም ህር፡
በወረቀቱ ላይ ጽሑፉን ልሞ ክር፡
እርሱ የሚፈጥነው በመቃብር ነበር ፡፡

፭. ጳጳሳቱ ሁሉ ስርአት ለመወሰን ከሩቅ እየመጡ፡፡
ርዕሰ መምህሩ ለምን ጠፋ ጌጡ፡፡

፮. ድጓ ጾመ ድጓ ዝማሬ መዋስዕት ዚማ በያይነቱ እየተነገረ፡
የቅኔው ባለቤት ሥርጋዌ ነበረ፡፡

፯. ማሰሪያው መቃብር መሆኑ ታወቀ፡
ዘርፍ ደፊ ሞት ነው ሙያው ተጠየቀ ፡፡

፰. የአለአዛር መቃብር እድለኛ ነሽ፡፡
ሰኔ ስምንት ቀን ከሊቃውንት ሁሉ ሥርጋዌ አገኘሽ
አብቤ ለምልሚ እንግዲህ

# ቅዱስ ሩፋኤል ለጦብያ

የእሳት ቃጠሎ በሚነግበት ወቅት ማንንም ማን ሳይለይ ደረቁ ንም እርጥቡንም አብሮ እንደሚያ ቃጥል ሁሉ ክፉዎች ሰዎች በሥሩ

ልበሽ፡፡

፱. በጣም የተማረው ያቤል ሞት ተማሬ፡
ስርጋዌን አገኘ ተመረቀ ድግሬ፡፡

፲. የታቦቱ ጥላ መጐናጸፊያውም የተገዛው ለክብር
መርገፉ ነው እንጂ ጌጡ ጥሩ ነበር ፡፡

፲፩. እናንት ካህናቱ አሸኛኘት አርጉ ተባበሩ በጣም፡
እንግዲህ ሥርጋዌ ተመልሶ አይመጣም ፡፡

፲፪. በስልጣን ላይ ሲሆን ያ ተክለ መድኅን
አጃቢ አይፈልግም ሲሄድ ብቻውን
ሄጄ እጠይቃለሁ መኖሪያ ቤቱን ፡፡

፲፫. የቀስተ ደመና ምልክት አለ በት፡
ቂልፉን አስገብቶ ብቻውን ገባበት ፡፡

፲፬. የማኅደረ ስብሐት ሀንፃው ጥሩ ነበር ደግሞ አቀማ መጡ፡
ቀለም የተቀባው ወደፊት አለ ጌጡ ፡፡

፲፭. ቃል ኪዳን ግቡለት ለተክለ መድኅን መሬት እንዲከፈል ክርስትና አባቱ የአቤል ሞት በቃል ፡፡

ሊቀ ጠበብቱ አሸቱ ጉሹ ከደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገ/ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

ትም ክፋትና በደል ምክንያት ብዙ ደጋግ ሰዎች ይማረካሉ ለመ ከራም ይጋለጣሉ ፡፡

ለምሳሌ የእሥራኤል ልጆች በሠሩት ኃጢአትና በፈጸሙት በደል ተማርከው ወደፋርስ ባቢ ሎን ሲወርዱ ኃጢአትን ያልሠሩ በበደል ያልተገኙ እነ ነቢዩ ኤር ምያስ ከእነሱ ጋር ተማርከው ፋርስ ባቢሎን ወርደው እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡

በዚህ አንጻር ጦቢትም ስልምና ሶር በነነዌ ንግሥ በነበረበት ዘመን ከሀገሩ ተማርኮ ወደ ነነዌ ሀገር እንደ ሄደና በዚሁም በነነዌ ቤት ሠርቶ ትዳርን መሥርቶ ሀብትንና ንብረትንም አበጅቶ ሲኖር አንድ ልጅ ወልዶ ነበር ፡፡ የልጁም ስም ጦብያ ይባላል ፡፡

ጦቢት እጁ ከመመጽወት የማ ያርፍ ምጽዋትም ከሞት የምታ ድን መሆንዋን የተገነዘበ ደግ ሰው ነበር ፡፡

ታድያ ጦቢት የተቸገረውን መርዳት ገንዘብ ላጣም ማበደር ልማዱ ስለ ነበር አንድ ጊዜ ገንዘ ቡን ራጉኤል ለተባለ ሰው በአደራ ሰጠው ፡፡

ይሁን እንጂ ጦቢትና ራጉኤል የነበሩበት ቦታ እጅግ የተራራቀ በመሆኑና ራጉኤልም በክፋት ሳይ ሆን ከሀገር ርቀት የተነሣ ሳይሰ ጠው ወይም ሳይልክለት ስለ ቀረ ሰውን ልኮ ገንዘቡን ለማስመጣት ግድ ሆነበት ወደዚያው የሚላክም ከልጁ ከጦብያ በቀር ሌላ ሰው ስላልነበረውና ጦብያም ራጉኤል ያለበትን ሀገር ስለማያውቀው አብሮት የሚሄድና መንገዱን



www.ethiopianorthodox.org

የሚያሳየው ሰው አስፈለገ ፤ በዚህ ጊዜ ጦቢት ልጁ ጦብያን ጠርቶ ወደ ራጉኤል ልልክህ ነበር ስለ ዚህ አብሮህ የሚሄደውን ሰው ብትፈልግ አለው ጦብያም ታዛዥ ልጅ በመሆኑ እሺ እፈልጋለሁ ብሎ ከቤቱ ወጣ እንዳለ አንድ ወጣት መንገደኛ መስሎ ቅዱስ ሩፋኤልን አገኘና ወዴት ትሄዳ ለህ ቢለው ራጉኤል ወዳለበት ሀገር የሚሄድ መሆኑን ከገለጸለት በኋላ ወደ አባቱ ተመልሶ አብሮኝ የሚሄድ ሰው አግኝቻለሁና መር ቀህ አስናብተኝ ልሂድ አለው ጦቢትም አንዴት ያለ ሰው ነው እስቲ ጥራው ብሎ አስጠርቶ ከየት እንደመጣ ወዴት እንደሚ ሄድ ሁኔታውን ካወቀ በኋላ በል ይህ ልጅ አብረህ እንዲሄድ አደራ እስጥሃለሁ ገንዘብንም እሰጥሃለሁ ብሎ ሁለቱንም አስናበታቸው እነ ሱም ጉዞአቸውን ቀጠሉና ሙሉ ቀን ሲሄዱ ከዋሉ በኋላ ጤግሮስ ከተባለው ታላቅ ወንዝ ሲደርሱ ጊዜ መሽባቸውና ከዚያ ለማደር ወስኑ ሙሉ ቀን ሲሄዱ ስለዋሉና ጦብያም ደክሞት ስለነበር ሊታ ጠብ ወደ ወንዙ ወረዶ ሲታጠ ብም ዓሣ ሊውጠው ተወርውሮ መጣበት ሁለቱም ግብግብ ተያ ያዙ በዚህ ጊዜ ቅዱስ ሩፋኤል ጦብያን አይዞህ ያዘው አትልቀ ቀው አለው ጦብያም ያንን ዓሣ እየጐተተ ከየብስ አወጣው ከዚህ በኋላ በል እረደውና ጉበቱን ልቡ ንና ሐሞቱን አውጥተህ ያዘው አለው ጦብያም መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል እንደ ነገረው ጉበቱን ልቡንና ሐሞቱን አንድ ላይ አድ ርጎ ያዘው ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ጦብያ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል መሆኑን አላወቀም ነበር ፤ ከዚያ አድረው በነጋታው ማልደው ተነ ሥተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ሲሄዱ የዓሣውን ጉበት ልብና ሐሞት ለምን አገልግሎት እንደ ሚውል ጦብያ ቅዱስ ሩፋኤልን ጠየቀው ። እሱም ይህ የያዝከው ጉበትና ልብ አሁን ከምንሄድበት ቤት የራጉኤል ልጅ ሣራ የምት ባል አለች መንፈስ ርኩስ አድሮ ባት ሰባት ባሎች ገድሎባታል ስለዚህ ይህ የያዝከውን ልብና ጉበት ሲያጤሱበት ይጠፋል አሁ ንም ያችን ልጅ አንተ እንድታገ ባት ይሆናል ። ሲለው ጦብያ እጅግ ተደሰተ ።

ሲሄዱ ውለው ከራጉኤል ቤት ሲደርሱ ተወክሮ ነግድ ልማድ አድርጎ የሚኖረው ራጉኤል በክ ብር ተቀብሎ የሚበሉትንና የሚ ጠጡትን ሲያቀርብላቸው ጦብያ ያከመንገድ የነገርከኝ ነገር ሳይፈ ጸም እህልንም አልቀምስም አለ።

ከዚህ በኋላ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ራጉኤልን እንዲህ አለው ይህ ልጅ የወንድምህ የጦቢት ልጅ ነው ። አሁንም ይህችን ልጅህ ሣራን ሚስት ትሆነው ዘንድ እንድትሰጠው ይለምንሃል አለው ። ራጉኤልም ደግና አውነ ተኛ ሰው ስለ ነበር መስጠቱን እስጥህ ነበር ነገር ግን ከዚህ በፊት ሰባት ሰዎች አግብተዋት ሰባቱም ሙተው እያደሩ እነሆ ብቻዋን ናት ያለችው ስለዚህ እሱም እሞ ታለሁ ብሎ ካልፈራ ስጥቼዋለሁ አለው በዚህ ጊዜ ውላቸውን ከፈ ጸሙ በኋላ በልተው ጠጥተው ሲያበቁ ጦብያና ሣራ ከሜጉላ ቸው ገቡ በዚህ ጊዜ ጦብያ ሳራን በዩ. እሁቴ እግዚአብሔር ኃብቻች ንን እንዲባርክልን ጸሎት እናድ ርግ አላትና ጸሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ያንን የያዘውን የዓሣ ጉበትና ልብ ቢያጤስበት በሳራ አድሮ የነበረው አስማንድዮስ የተባለው ጋኔን እንደ ጢስ ተኖ እንደ ትቢያ በኖ ጠፋ ራጉኤል ግን እንግዲህ ይህም ልጅ ሳይሞት አይቀርምና መቃብሩን ቆፍሬ ልምጣ ብሎ ማልዶ ተነሥቶ መቃብሩን ቆፍሮ ተመልሶ ሙሽሮቹ ካሉበት ቤት በር አንኳኩቶ እንዴት አደራችሁ ቢላቸው ደህናነን እግዚአብሔር ይመስገን የሚል ድምፅ ሰምቶ በጤና ያሳደራቸው ልዑል እግዚ አብሔር ክብር ተመስገን ብሎ ምስጋና አቀረበ ። ተመልሶ ሄዶም ያንን የቆፈረውን መቃብር ደፈ ነው ።

የልጁ የሣራ ሠርግም እንደ ተሳካላትና ያገባትም ልጅ በጤና ማደሩን አይቶት ፲፬ ቀን አብረውት እንዲሰነብቱ ቅዱስ ሩፋኤልን ለመነው ቅዱስ ሩፋኤልም ልመና ውን ሰምቶ ፲፬ ቀን አብረው እንዲ ሰነብቱ ፈቃዱ ሆነ ።

፲፬ ቀን ከሰነበቱ በኋላ ቅዱስ ሩፋኤል ጦብያንና ሣራን ይዞ ወደ ጦቢት ጉዞውን ቀጠለ የራጉኤል ሚስት ግን ልጇ ጠፋ ፡ ልጇን ምን ዋጠው እያለች እጅግ ተቸግራ ነበር ።

ከዚህ በኋላ ከቤታቸው እንደ ደረሱ ጦቢት ልጅህ መጣ ሲሉት ዓይኑ ጠፍቶ ነበርና ከተቀመጠ በት ሁኖ በዳበሳ ልጄ እንኳን ደህና መጣህ ሲለው ጦብያም ሊስ መው ወደ እሱ ቀረበና የዓሣውን ሐሞት ዓይኑን ቢቀባው ጨርሶ ጠፍቶ የነበረው በራለት ጦቢት ጠፍቶ የነበረው ዓይኑ ሲበራለት በደስታ ላይ ደስታ ተጨመረለት።

እንግዲህ ከጦብያ ጋር የሄደው ማን እንደ ሆነ ጦቢትም ሆነ ጦብያ አላወቁም ነበር ቅዱስ ሩፋ ኤል ግን ጦብያን መልሶ ከአባቱ ጋር ካገናኘው በኋላ እኔ ማን መሆ

(ወደ ገጽ ፰ ዞሯል)



## ዘመን ሲለወጥ

የያዝነው ዘመን አልፎ አዲስ ዘመን ሲለወጥ ባለፈው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ለውጥ እንዳሳየች ምን እንደሰራች አሠሪዎቿ ምን እንዳሠሩ ሠራተ ኞች ምን እንደሠሩ ዘወር ብለን መመልከት ያስፈልገናል ። ባለ ፈው በ፲፱፻፹፩ ዓ ም በማቴዎስ ዘመን ምን እንደተሠራ ምንለ ውጥ እንደታየ አሮጌው እንደታ ደሰ አዲስም ነገር እንደተሠራ ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ምን ግንኙነት እንደተፈጸመና ጉብኝት እንደተደረገ ገምግመን ካላወቅን በሚለወጠውም በአ ዲሱ ዘመን በዘመነ ማርቆስ ሊሠራ የታቀደ ፕላን መኖሩን ካልተረዳን ዘመን ተለወጠ እን ኳን ለአዲሱ ዘመን አደረስህ እያሉ መነጋገሩ ብቻ አይበቃም ። ቤተ ክርስቲያንም ዘመን ሲለወጥ "ማቴዎስ ተሻረ ማርቆስ ተሾመ" እያለች የምታውጀው አዋጅ በተ ግባር ተገልጾ ካልታየ የልማድ ስለሚሆን ቃል ብቻ ሆኖ ከመቅ ረት በቀር ውጤት አይታይበ ትም።

አበው ሲመስሉ "በዮሐንስ እረስ በማቴዎስ እፈስ" የሚል ዘይቤአዊ አነጋገር አላቸው እንደ ተባለውም ባለፈው በዘመነ ማቴ ዎስ ቤተ ክርስቲያናችን በመንፈ ሳዊ መሪዎቿና አባቶቿ እንዲሁም አሠሪዎችና ሠራተኞች መካከል እያሉ የሥራ ፍሬዎች ታይተዋል ከነዚህም ጎላ ያሉትን ብንጠቅስ ፤

፩ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መር ቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለአድባራት አስተዳዳሪዎች ፡ ለቤተ ክህነት ሠራተኞች የሥራ መመሪያ ሰጥተ ዋል ። ቅዱስነታቸው ይህን የሥራ መመሪያ የሰጡት መስከ ረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ ም በመን በረ ፓትርያርክ ስብከተ ወንጌል አዳራሽ ነው ።

ቅዱስነታቸውም በሰጡት የሥራ መመሪያ የአ.አ.አድባራ ትና ገዳማት በሕግ ተጠናክረው አብበዋል ።"በሕግ አሽብርተ ዋል፡ ፍሬ ታይቶባቸዋል ። እግዚ አብሔርን በሚወዱና በሚፈሩ ምዕመናን ታቅፈዋል ፤ በየዕለቱ ቅዳሴ ውዳሴ የማይለይባቸው አብ ያተ ክርስቲያናትም በብዛት አሉ ፡ ይህ ሁሉ የሚያስደስትና የሚያስ መሰግን ነው ነገር ግን ለዚህ በጐ አላማ ሰውና እግዚአብሔርን በተ ልዕኮአቸው ደስ የሚያሰኙ በህግ የሚመሩ ዲያቆናት አሉ ስንል እንዳሉም እንደሌሉም ይታየናል፡ ካሉ በኋላ ማንኛውም ቤተ ክርስ ቲያንን አገለግላለሁ ብሎ የተሰ ለፈ ሁሉ የተመደበበትን ሥራ በታማኝነት ማከናወን ይኖርበ ታል የሚል መመሪያ ሰጥተዋል ።

፪ኛ. ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ ም የመንበረ ፓትርያርክ አጠ ቃላይ ስበካ ጉባኤ አያሌ ውሳኔዎ ችን አስተላልፏል ። ከውሳኔዎ ቹም መካከል ስለስብከተ ወንጌል በቁጥር ፲ በፊደል ተራ "መ" ስለጋዜጦችና መጽሔቶች ህት መት ሥርጭት ከተልዕኮውም አንዱ የእምነትና ሥነ ምግባር ትምህርት ማስረጫ የሆኑ ጋዜጦ ችንና መጽሔቶችን ምዕመናኑ በየ ጊዜው እንዲያገኙ ማድረግ ነው ። ስለዚህ እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ከሀገረ ስብከቱ አጠቃላይ የሰበካ ገቢ ላይ ጋዜጦችና መጽሔቶች ህትመት የተወሰነ ገንዘብ እንዲ መደብ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው የአ. አ.ገዳማትና አድባራት እያንዳንዳ ቸው የአንድ አገልጋይ ካህን ደመ ወዝ ያህል ገንዘብ ለጋዜጦችና መጽሔቶች ስርጭት እንዲመ ድቡ በመወሰኑ የቤተ ክርስቲያ ንን የሥራ አመራርና የጉባኤውን ብስለት ለችግሩም መፍትሔ ሰጪ መሆኑን ያሳያል ።

፫ኛ. በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የሚመራ የልዑካን ቡድን በምዕራብ ጀር መን ፡ በጄኔቫ ፡ በኢየሩሳሌምና በግሪክ የተለያዩ የሃይማኖት ድር ጅቶችን ፡ አብያተ ክርስቲያናትን በመጐብኘት ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር ስለሰላም ፡ ስለአብ ያተ ክርስቲያናት አንድነት ፡ ስለ ልማትና ስለማኅበራዊ አገልግ ሎት ውይይት ከሚያዝያ ፳፩ እስከ ግንቦት ፲፩ ድረስ ከላይ የተጠቀሱትን አገሮች ጐብኝቶ ተመልሷል ። የጉብኝቱም ዋና ዓላማ በትግማች አብያተ ክርስቲ ያናት መካከል መልካም ወዳጅ ነት እንዲፈጠር መግባባት መረዳ ዳት እንዲኖር ለማድረግ ነው ።

በተለይም ከጀርመን ወንጌላ ዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር ወደፊት ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት በማ ስመልከት እናትና አባት የሌላቸ ውን ህፃናት በመንከባከብ ፡ የነዋ ናት ማሰልጠኛ ተቋሚትን በማጠ ናከርና ለልማት ፕሮጀክቶች ድጋፍ በመስጠት ትብብር ቢደ ረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፍላጐት እን ደሆነ ቅዱስ ፓትርያርኩ በስጡት መግለጫ አስረድተዋል ። የወንጌ ላዊት ቤተ ክርስቲያንም መሪዎች በተጠየቁት ሁሉ የሚረዱና የሚ ያግዙ ለመሆናቸው ቃል ገብተ



www.ethiopianorthodox.org

ዋል ። ይህም ለቤተ ክርስቲያኗ ፍሬያማ ጉብኝት ማስገኘቱንና የተቀደሰ ጉዞ መሆኑን ያበስራል ።

እንግዲህ የኢ.ት.ኦ.ተ.ቤ. በየዘመናቱ ያ' በተቻቸውን ሥነ ጽሑፎች ፡ ምርጥ እቃዎች ልዩ ልዩ ጌጦች ፡ የባሕልና የቅርስ መዘክሮች ለትውልድ ማስረከቧን ከማሳየቷም ባሻገር በዘመን የምትሠራና ዘመንን ለሥራ የምትለውጥ ለመሆኗ ሥራዋ ምስክር ስለሆነ በዘመን ሥሩ እያለች ታስተምራለች ። ሰዎች በዘመን መሥራት እንደሚገባቸው ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርአ ያዕቆብ ሲናገር "ዘመንን አትርገሙት የዘመን ደግና ክፉ የለውም ። ዘመን እንዲ ክፉ የሚያደርጉት ሰዎች ናቸው ደግ እንዲሆንም የሚያደርጉት ሰዎች ናቸው ። ሰዎች በዘመን አሉ እንጂ ዘመን በሰው ውስጥ የለም ዘመንን የሚለውጡት ሰዎች ናቸው ሰዎች ግን በዘመን አይለወጡም ብሏል ።

እንዳለውም ሰዎቹ በዘመን ከሠሩበት ዘመን ከሕብረተሰቡ ባህላዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም ጋር የተያያዘ መንፈሳዊ ክብር የሚጎበረቅበት የሥራ ፍቅር የሚገለጥበት የአገር ዕድገት የሚገኝበትና ብልጽግና የሚታፈስበት ታላቅ ኃይል ነው ። ይኸውም ዘመን የወጣውን ጉላን ተከትሎ ከሠሩበት የተትረፈረፈ በርከት እንደማያስገኝ ለማንም የተሰወረ አይደለም ። ይህ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ካለፉት ጊዜያት ይልቅ በአዲስ ዘመን ላቅ ያለ የዕድገት ለውጥ የምታካሂድበት ሊሆን ይገባል ።

ስለዚህ ምዕመናንን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ፡ በሰባክ ጉባኤ ፡ በገንዘብ አስተዋፅኦ በኢኮኖሚያዊ ተግባራትና በማኅበራዊ ጉዳዮች በኩል ንቁ ተሳትፎ ይፈለግባቸዋል ። ይህ ከተደረገ ቤተ ክርስቲያን የዜጐቿን መንፈሳዊ መብትና መንፈሳዊ ነፃነት የሚያስከብር መንፈሳዊ ኃይል ይኖራታል ። በተጨማሪም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በዓላማ አንድነት የቅርብ ግንኙነት እንዲያደርጉ አመቺ መንገዶችን ለመቀየስ ያስችላታል ። በዚህ አኳኋን አመቺ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ የምዕመናንን ንቁ ተሳትፎ ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ኃይል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በዓለም ላይ በክርስትና እምነት ከታወቁ ሀገሮች አንዷ ስትሆን ሕዝቧም ለረጅም ጊዜ በየዓመቱ ዘመንን በዘመን እየለወጠ ባህሉን እያከበረ ሥርዓቱንና እምነቱን ጠብቆ ነፃነቱን አስከብሮ የኖረ ጠንካራ ሕዝብ መሆኑን ታሪክ ሲመሰክርለት ይኖራል። በመሆኑም ዘመንን ተከትሎ በመስራት ከጊዜ ወደ ጊዜ የዕድገቱን አቅጣጫ እያሻሻለ በማሳየት ብዙ ዘመናትን አሳልፏል ። ቤተ ክርስቲያናችን በምትሰጠው አመራርና ቃለዓዋዲ ደንብ የምዕመናኑ የሥራ ተካፋይነትና የሥልጣን ባለቤትነትዕውን የሆነበት ዘመን በመሆኑ ያለፉት ዘመናት ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን የእድገት መሻሻል የታየባቸው ዘመናት ናቸው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም ።

በዚህም ማንኛውም የቤተ ክርስቲያኗ ተከታይ የሆነ ሁሉ በተሰጠው ቃለአዋዲ ደንብ ራሱን በራሱ ለመምራት ችሏል የራሱ መሪና አስተዳዳሪም ለመሆን በቅቷል ለጋራ ብልፅግናው አጋዥ ሐሳብ የማፍለቅ የመወሰንና ውሳኔውንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መንፈሳዊ ሥልጣን ተቀዳጅቷል ።

ስለዚህ የተረከበውን ኃላፊነት በብቃት የሥራ ፍሬ ውጤት ለማሳየት አስፈላጊውን መሥዋዕትነት ሁሉ በመክፈል በያዝነውም አዲስ ዘመን አዲስ መሠረት መጣል ያስፈልጋል ። ባለፈው ዘመን እንደተሠራው አሁንም በአዲሱ ዘመን ከተሠራ የእድገትንም ለውጥ ከማጠናከር ጋር መንፈሳዊ ሥርዓትን ለማስፈን የተጀመረው እንቅስቃሴ አዲስ የሥራ ፍሬ እንደሚያሳይ አያጠራጥርም።

እነዚህ የሰባካ ጉባኤ አባሎች ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት የተመረጡት እንዲህ በቀላሉ አይደለም ። በሥራ ወዳድነታቸው ፡ በቅንነታቸው በታማኝነታቸው በቤተ ክርስቲያን አባልነታቸውና በመንፈሳዊነታቸው ልቀው በመገኘታቸው ነው ። እንደተባለውም የሰበካ ጉባኤ አባላት ባለፉት ዘመናት የሚጠበቅባቸውን የሥራ ኃላፊነት በሚገባ ተወጥተዋል ። የምእመናኑን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት ለማሻሻልና ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ የወጡትን መርሐ ግብሮች በመከተል በአዲሱም ዘመን ሠርተው ማሠራት ይጠበቅባቸዋል ስለዚህ በአዲሱም ዘመን ሥራችን እንዲቃና ሰላም ይሁን ለሁላችን ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# የአባ ገብረ ጻድቅበሻህ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ

**አባ ገብረ ጻድቅ በሻህ ከአባታቸው ገራዝማች ብርሌ ከእናታቸው ወ ር ቀነብሽ በ፲፱፻፲፰ ዓ ም በጎጃም ሀገረ ስብከት በባሕር ዳር አውራጅ ይልማና ደንሳ ወረዳ ወንጨር ቅ ጊዮርጊስ ተወለዱ ።**

**ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወንጨር ቅ ጊዮርጊስ ገዳም ከነበሩት መሪጌታ ቢሠጡር ከተባሉት የድጓ መምህር ትምህርት ጀምረው ጻዊት ደግመው ፀዋትወ ዜማም ተምረው ከጨረሱ በኋላ በ፳ ዓመታቸው ወላጆቻቸው ሚስት አጩላቸው እርሳቸው ግን ሚስት ለማግባት ፈቃደኛ ስላልነበሩ ለወላጆቻቸው ደጋግመው ገለጹላቸው ቢሆንም ወላጆች አባባቸውን አልተቀበሏቸውም አባ ገብረ ጻድቅም ፈቃዳቸውን ለመፈጸም ሲሉ ለጊዜው እሺ አሉና ሠርጉ ተሠርጐ የተጠራው ሰው እንደተሰበሰበ እንደ ጻድቁ ገብረ ክርስቶስ መንነው ሂደው ክብራቸው እንዳይገለጽ ሕመምተኛ መስለው ግርግ ሌሊቱን ድምፀ አራዊቱን ቁረ ሌሊቱን ሐሩረ ፀሐዩን ችለው ደረቱ አርባዕቱ እንስሳ ከተባለው ቤተ ክርስቲያን ፯ ዓመት ኑረዋል ።**

**ከዚህ በኋላ እንደገና ወደተወለዱበት ወንጨር ቅ ጊዮርጊስ ገዳም ተመልሰው ጥቂት ጊዜ እብድ መስለው ኑረዋል ። እንዲሁም በቆለላ ቁስቋም ክኮሬ አቦና በሌሎችም አድባራት በመዘዋወር ፰ ዓመታት ያህል አስተምረዋል ።**

**የወንጌልን ቃል በንቃትና በትጋት በማስተማራቸው ብዙ ሰዎች ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ተመልሰዋል ።**

ድውይ በመፈወስ ለምጽ በማንፃት ጋኔን ከሰዎች በማስወጣት **ልዩ ልዩ ተአምራት ያደርጉ ስለነበር** ዝናቸውን የሰሙ በሽተኞች ሁሉ ወደ አባ ገብረ ጻድቅ እየ



አባ ገብረ ጻድቅ በሽተኛውን ሲያጠምቁ

መጡ ያፈውሱ ነበር ከሠሯቸው ተአምራት ለማስረጃ ያህል ጥቂቶችን ተጥለን እንመልከታቸው ።

፩· ከዕለታት አንድ ቀን አንድ አባ ጽጌ የተባሉ መናኒ ዜና ተአምራታቸውን ሰምተው ከደብረ ጽላልሽ ተነሥተው ወደ አባ ገብረ ጻድቅ መጡ አባ ጽጌ ከትከሻቸው ላይ የበጥ በሽታ ነበረባቸው ወዲያው እንደደረሱ በእጃቸው ትከሻቸውን ነካ ነካ ቢያደርጓቸው እበጡ ውልቅ ብሎ ወድቆ ጤነኛ ለመሆን በቅተዋል ።

፪ኛ· አባ ገብረ ማርያም የተባሉ መናኒ በእንቅርት በሽታ አንገታቸው ተቆልምሞ እህል ለማላመጥና ለመዋጥ ተሸንፈው ሳሉ ከአቾፈር ወረዳ ለባ ማርያም ከተባለች ደብር ተነሥተው መጥተው ከአባ ገብረ ጻድቅ እጅ ምግብ ተቀብለው ቢቀምሱ ያ እንደታላቅ ድንጋይ ተጕልቶ ሲያሰቃያቸው የነበረው ዕንቅርት ከዚህ ደረስ ሳይባል እንደጨው ሟሙቶ ጠፍቶላቸዋል ።

፫ኛ· እኒሁ አባት አባ ገብረ ማርያም ዓይናቸውን ታመው እንኳስ በጨለማ በቀንም ማየት ተስኗቸው ሲጨነቁ ቢዳስሷቸው ተፈውሰ ።

፬ኛ· በዚሁ ወረዳ ቆለላ (ጉርጅ ባሕር) ኗሪ የሆኑ አባ ዓይናለም የተባሉ መነኩሴ በየሐኪም ቤትና መድኃኒት አውቃለሁ በሚለው ሰው ሁሉ እየዞሩ ቢታከሙና መድኃኒትም ቢያደርጉ ሳይፈወሱ በመቅረታቸው ፯ ዓመት ሙሉ እንደ እንጨት ደርቀው ከኖሩ በኋላ ወደ አባ ገብረ ጻድቅ መጥተው ምግብ ባርከው ቢሰጧቸው



www.ethiopianorthodox.org

ያንን ቀምሰው ከደዌያቸው ተፈውሰዋል ጥቂቶቹን መናገራችን ነው እንጂ በአባ ገብረ ጻድቅ ጸሎት የተፈወሱት በሽተኞች በዚህ ጠባብ ዓምድ ተዘርዝረው ቢጻፍ ቦታ ሊበቃቸው አይችልም ነበር ።

አባ ገብረ ጻድቅ በገድላቸው በትሩፋታቸው በጸሎታቸው በሽተኞችን በመፈወስ ቆለላ ከተባለች ቤተ ክርስቲያን ፵፯ ዓመት ግርማ ሌሊትን ድምፀ አራዊትን ታግሠው የክረምቱ ማዕበል በላይ በታች እየፈሰሰባቸው መከራን ሲቀበሉ ከኖሩ በኋላ "ሠናይ ለብእሲ ለእመ ይከውን መቅበርቱ ውስተ ርስቱ" እንደተባለ እንደ ገና ወደ ተወለዱበት ቦታ ተመልሰው ወንጨር ቅ/ጊዮርጊስ ከተባለው ገዳም ፬ ዓመት ከመቃብር ላይ ወድቀው ረቂቅ በሆነ መንፈሳዊ ጸጋቸው ሕሙማንን እየፈወሱ ሕያዋንን እየመከሩ ከቆዩ በኋላ ሰው ሆኖ ከሞት ማምለጥ አይቻልምና በ፸፱ ዓመታቸው ፲፱፻፹ ዓ ም ጥር ፳ ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

ካህናቱ ለጸሎተ ፍትሐት ተሰብስበው ሲጸልዩ ልብን የሚሠልብ የዕጣን መዓዛ ከአስከሬኑ ትጉልል ትጉልል እያለ ሲወጣ በመታየቱ በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ በከፍተኛ አድናቆት ተውጦ ነበር ።

ለአባቶች የሚደረገው ሥርዓተ ጸሎት ከተደረገላቸው በኋላ ሥርዓተ ቀብራቸው በገዳመ ሳሙኤል ወንጨር ፡ ቅ ጊዮርጊስ ከቀኑ ልክ በ፱ ሰዓት ተፈጽሟል ከሥርዓተ ቀብሩም በኋላ የአባ ገብረ ጻድቅ የሕይወት ታሪክ ለተሰበሰበው አዘንተኛ በንባብ ተሰምቷል ።

ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ አባቶች በየስጦታቸው መሆኑ አያጠያይቅም ሐዋርያው ጳውሎስ "እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር አገልግሎትም ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ "ብሏል ሮሜ ፲፪.፮ ሐዋርያው እንደተናገረው ሁሉም በተሰጠው ጸጋ ቤተ ክርስቲያንን የማገልገል ግዴታ አለበት ይኸው ሐዋርያ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "ለአንዱ ተአምራትን የማድረግ ለአንዱም ትንቢትን የመናገር ለአንዱም መናፍስትን የመለየት ወዘተ ይሰጠዋል ይላል ፩ኛ ቆሮ.፲፪.፲

ስለዚህ ሁላችንም በየችሎታችንና በየስጦታችን እግዚአብሔርን ማገልገል ይገባናል እኚህ የተጠቀሱት አባት አባ ገብረ ጻድቅ ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ጸጋ እየሠሩ እንዲኖሩ የተወሰነላቸውን ዘመን ፈጽመው አልፈዋል ። አምላክ በሰጠው ስጦታ ሠርቶ መሄድ ያስመሰግናል በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስወቅሠው በስጦታ አለመሥራት ነውና እንደ አባ ገብረ ጻድቅ በስጦታችን ጠንክረን ሠርተን ከፈጣሪያችን ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋን ለመቀበል ያብቃን።

የዜናው አቅራቢ
ከደቀ መዛሙርቶቻቸው አንዱ
አባ ጽጌ

# "ቅዱስ ዮሐንስ"

ዮሐንስ ማለት የእግዚአብሔር ጸጋ ማለት ነው ። በዚህ ስም የተጠሩና የሚጠሩ ብዙ ናቸው ። ከነዚህም መካከል በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኛቸው መጥምቁ ዮሐንስ ፡ ሐዋርያው (ወንጌላዊው) ዮሐንስ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ይባላሉ ። በዚህ ጽሑፍ የተገለፀው ግን መጥምቁ ዮሐንስ ነው ዮሐንስ ከክርስቶስ ጥምቀት በፊት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ለመመለስ በነቢዩ ኢሳይያስ "እነሆ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ" ተብሎ በተነገረው ትንቢት አስቀድሞ የተላከ ነው ። (ማቴ. ፲፩፡፲ ማር ፩ ፡፪—፫) ቅዱስ ዮሐንስ በመልአኩ በቅ ገብርኤል አብሳሪነት ከዘካርያስና ከኤልሳቤጥ በእርጅና ዘመናቸው የተወለደ ሲሆን እርሱም በእናቱ ማኅፀን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ጌታውንና አምላኩንም አውቆ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አክስትዋን ኤልሳቤጥን ለመጠየቅ ከናዝሬት ወደ ተራራማው አገር ወደይሁዳ ከተማ ወጥታ ሰላምታ ስታቀርብላት ዮሐንስ በእናቱ ሆድ ሆኖ ሦስት ጊዜ ዘለለ (ሰገደም) ። ኤልሳቤጥም የእግዚአብሔር ቸርነትና የእመቤታችን ቅ ድንግል ማርያምም ቅድስና በማድነቅ የክብር ሰላምታ አቀረበችላት (ማር. ፩—፫ ፡ ሉቃ. ፩ ፡ ፲፭—፵፩ ።)

ዮሐንስ ከሕፃንነቱ ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሔር መንግሥት አስተማሪና አብሳሪ እንዲሆን የተጠራ በመሆኑ ከእናት ከአባቱ ተለይቶ በምድረ በዳ በብሕትውና ይኖር ነበር ። ልብሱም የግመል ፀጉር እንደበርኖስ የተሠራ ሲሆን ምግቡም አንበጣ የሚባል የዱር ጋጃ ማር በመጠኑ እየተመገበ የሚኖር ነበር በሰው እጅ ከተሠራው ከላመ ከጣመ የራቀና ድምፀ አራዊትን. ጸብአ አጋንንትን ታግሶ ከሰው ተለይቶ በምድረ በዳ በብሕትውና የሚኖር ነበር ።

የዮሐንስ ብሕትውና በዘመናችን እንደምንመለከታቸው ከአፍቅሮ ንዋይ ፡ ከነገረ ዘርቅ ፡ ከማታለልና ከማጭበርበር ከመሰርይ ግብር ሁሉ የራቀ በሃይማኖቱና በምግባሩ የጸና የቀና ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ምስክር ሆኖ የቆመ ነበር ።

ዮሐንስ በሚሰጠው ትምህርትም ዘኢያደሉ ለገጸ ሰብእ እንደነበር ቅዱስ ሉቃስ በቅዱስ ወንጌሉ የዘገበው ኃይለ ቃል ይመሰክርልናል ። ይኸውም ሕዝቡ ተሰብስቦ ትምህርቱን ካዳመጠ በኋላ ምን እናድርግ ብለው ጠየቁት እርሱም ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ይስጥ ፡ ምግብም እንደዚሁ ያካፍል አላቸው ቀራጮችም ቀርበው መምህር ሆይ እኛስ ምን እናድርግ? ብለው ላቀረቡለት መጠይቅ ሳይፈራና ሳያፍር በድፍረት ከታዘዛችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ ሲል አስጠነቀቃቸው፡ ጭፍሮቹም ደግሞ ቀርበው ተመሳሳይ ጥያቄ አቀረቡለት ዮሐንስም በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ ፡ ደመወዛችሁ ይብቃችሁ ብሎ አስተማራቸው ።

ከዚህም ሌላ ዮሐንስ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ እንደተዘጋጀ ከእርሱም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመጣ ሰበከ እርሱም በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ፡ ሕዝቡን እንደሚያነፃ ገለጠ ። ዮሐንስ ሁል ጊዜ ራሱን ዝቅ የሚመጣውን ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ አድርጎ ሥራውን ይገልጽ እንደነበረ እንረዳለን ። (ዮሐ.፫ ፡ ፯—፲፯)

ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ሲያስተምር ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደእርሱ መጥቶ እንዲያጠምቀው ጠየቀው ። ዮሐንስ ግን "እኔ ከአንተ ልጠመቅ መምጣት ይገባኛል እንጂ እንዴት አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ? ሲል ትሕትናን በተመላበት አነጋገር ጠየቀው ። ጌታችን ግን አሁንስ ተው ይልቅስ አጥምቀኝ ብሎ ስላዘዘው አጥምቆታል ። ዮሐንስ ጌታን ካጠመቀ በኋላ "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ብሎ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ መልእክተኛ መሆኑን መስክሮ አረጋገጠ ። ከዚህ በኋላ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደተከተሉት አይቶ (ሰምቶ) በጣም ደስ አለው ። (ዮሐ.፩ ፡ ፳፱—፴፬ ዮሐ.፫ ፡፳፪ ፴ ።)

ዮሐንስ ሕዝቡን በንስሐ ከማጥመቁ በላይ የማስተማር ሥራውን አላቋረጠም ። ከዕለታት አንድ ቀን ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ማግባቱን አይቶ ስለወቀሰው ይዞ አሰረው ፡ በእስር ቤት እንዳለም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊመጣ ያለው መሲሕ መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንዲጠይቁት ሁለት ደቀ መዛሙርትን ላከ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻ ነቢይ መሆኑን መሠከረለት በመጨረሻም የሄሮድስ ሚስት በልጅዋ ዘፈን ምክንያት የዮሐንስን ራስ እንዳስቆረጠችው ቅዱስ ወንጌል ይነግረናል ደቀ መዛሙርቱም አንሥተው ቀብረውታል ። (ማቴ.፲፯ ፡ ፱—፲፫ ። ማር. ፮ ፡ ፲፬—፳፱ ።)

ሊቃውንት መተርጉማን ደግሞ የሄሮድያዳ ልጅ የዮሐንስን ራስ ካስቆረጠች በኋላ ራሱን ከባለወ ኃቹ በወጭት ልትቀበል በቀረበች ጊዜ ክንፍ አውጥቶ እንደበረረና ሰባት ዓመትም እየዞረ በየአሕጉሩ እንዳስተማረ ይናገራሉ ። ከሰባት ዓመት በኋላ ግን በአንድ ተራራ ላይ አርፎ እንደ እንቁ ሲያበራ ስለተገኘ አንሥተው ቀበሩት ይላሉ ።

መጥምቁ ዮሐንስ በገድል በሃይማኖት በትሩፋት ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ሲያገለግል ከኖረ በኋላ መስከረም ፪ ቀን በአረመኔው ሄሮድስ እጅ በሰማዕትነት አርፎአል ። የማያልፈውን የክብር አክሊልም ተቀዳጅቶአል በአማላጅነቱ የታመነ በስሙ ቁራሽ እንጀራ ያበላ ፡ ቀዝቃዛ ውኃ ያጠጣ ፡ ቤተ ክርስቲያን በስሙ ያነፀ በመንግሥተ ሰማያት ዋጋውን እንደማያጣ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተቀብሎአል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በትምህርቱ በተአምራቱ በምልክቱ በሃይማኖቱ ፡ በአማላጅነቱ ስለምታምን በስሙ ቤ. ክርስቲያን ሠርታ በየዓመቱ መስከረም ፪ ቀን ምትረተ ርእሱ ለዮሐንስ በማለት መታሰቢያውን በደማቅ ሁኔታ ስታከብር ትኖራለች ።

ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንና ምእመናትም የመጥምቁን አማላጅነት በማመን ቤ. ክርስቲያኑን እየሠሩ ፡ በስሙ ማኅበር እየጠጡ፡ ፀበል ጸዲቅ ለነዳያን እያበሉ እያጠጡ ፡ በዓሉን እያከበሩ ስለሚኖሩ በመንግሥተ ሰማያት የማያልፍ ክብርና በረከት እንደሚያገኙ የታመነ ነው ።

ስለዚህ ሁላችንም የመጥምቁ ዮሐንስን ትምህርትና ተአምራት በመመልከትና እምነትና አማላጅነት በመከተል እምነታችንን አጽ



www.ethiopianorthodox.org

# መስቀል ኃይላችን ነው

ማናቸውንም ሥራ ለመሥራት ኃይል ያስፈልጋል ፡፡ ኃይል ደግሞ እንዲሁ ስለማይገኝ ሥጋዊ ኃይል ለማግኘት ጥሩጥሩ ምግብ እንደ ሚያስፈልግ ሁሉ መንፈሳዊ ኃይልም ለማግኘት ጽኑዕ እምነትና ምግባር ያስፈልጋል ፡፡ ስለዚህ ነው "ያመነ ሁሉ በመስቀሉ ኃይል ይድናል ፡፡ መስቀል ኃይላችን ነው" ተብሎ የተጻፈው ፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በመለዕልተ መስቀል ላይ አሳልፎ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ መስቀሉ እንደፀሐይ እያበራ ፡ ሕሙማንን ሲፈውስ ፡ ሙታንን ሲያስነሣ፡ ብዙ ታምራትን ሲያደርግ ቆይቷል ፡፡ አይሁድ ይህንን ተመልክተው ክርስቶስን በቅንአትና በምቀኝነት ተነሣስተው እንደሰቀሉት መስቀልንም ወደከተማ ዳር ወስደው ጥልቅ ጉድጓድ በመቆፈር ቀብረውታል ፡፡ በላዩም ላይ የከተማ ጥራጊ ሁሉ እንዲደፋበት በማወጅ ከጥራጊው ብዛት የተነሣ የተቀበረበት ቦታ እስከሚጠፋ

---

ንተን እንኑር ፡ በማን ዘራሽ ሃይማኖትና በርካሽ ባሕል ከመታለልም ርቀን በትሩፋት አጊጠን የማያልፈውን ክብር ለመቀዳጀት በንስሐ ተመልሰን የክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን ተቀብለን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተዘጋጅተን እንጠብቀው ፡፡

ሊቀ ትጉሃን ገ/ክርስቶስ
ኃ/ማርያም

ድረስ ጋራ አሳክለው ቆልለውበታል ፡፡

ከዚህም በኋላ ንግሥት ዕሌኒ ወደ ኢየሩሳሌም መጥታ መስቀሉን ለማግኘት የተቀበረበትን ቦታ የሚያሳያት አጥታ ብዙ ከደከመች በኋላ አንድ አይሁዳዊ አሳይቷታል የሚሉም አሉ ፡፡ ነገር ግን ብዙ ዕጣን በእሳት አያይዛ ወደ እግዚአብሔር ብታመለክት የዕጣኑ ጢስ ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ ተመልሶ መስቀሉ ከአለበት ቦታ ላይ በመተከል (አርፎ) አሳይቷታል ፡፡ ወዲያውኑ ማስቆፈር ጀምራ መጋቢት ፲ ቀን ፫፻፳፯ ዓ/ም መስቀሉን አግኝታ ለማስወጣት ችላለች ፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ "ሰገደ ጢስ በኀበ ኀታ ዝደፈኑ አይሁድ ዮም ተረክበ ዕፀ መስቀል" በማለት ዘምሮ አል፡፡

ንግሥት ዕሌኒ መስቀሉን ካገኘች በኋላ እጅግ ተደስታ በዘመኑ የሮም ንጉሥ ወደነበረው ልጅዋ ወደ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ላከች ቆስጠንጢኖስም ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ በጎልጎታ ከእናቱ ጋር ታላቅ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው መስከረም ፲፯ ቀን መስቀሉን በማስገባት በክብር እንዲቀመጥ አደረገው ቅዳሴ ቤቱንም በታላቅ ድምቀት አክብሯል ፡፡

ከዚህም በኋላ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ መክስምያኖስ ከሚባለው ንጉሥ ጋር ሊዋጋ በተነሣ ጊዜ እንዴት አድርጎ ቢገጥመው ድል ማግኘት እንደሚችል ሲያስብ ሳለ፡ በራዕይ "በዝ ትማርት መስቀል ትመውዕ ፀረከ በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ታሸንፋለህ" የሚል ጽሑፍ በመስቀል ላይ ተቀርጾ እያበራ ታይቶታል ፡፡ ይህንንም እግዚአብሔር በቸርነቱ ያሳየው ኃይል መሆኑን አምኖ የወርቅ መስቀል አሠርቶ በግንባሩ፡ በፈረሱ ዕቃውና በጦር መሣሪያው ላይ የመስቀል ምልክት በማድረግ ዘምቶ ጠላቱን ድል በማድረግ በጠቅላላው ሮም ላይ ለመንገሥ በቅቷል ፡፡

በዚህም ዘመን በዲዮቅልጥያኖስ ጊዜ ተማርከው የነበሩትን የአብያተ ክርስቲያናት ሀብትና ንብረት ፡ ንዋያተ ቅድሳት አስመልሷል ፡፡ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትም ታድሰዋል ፡ ክርስቲያኖችም ሃይማኖታቸውን አስፋፍተው ፡ እምነታቸውን አጠንክረው በሰላም የኖሩበት ዘመን ነበር፡፡

እንደገናም ኢየሩሳሌም በቱርኮች እጅ ተይዛ በነበረበት ጊዜ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ለመጎብኘትና መስቀሉን ለመሳለም ከየመንግሥታቱ የሚመጡትን ክርስቲያኖች ቱርኮች ብዙ ግፍና ውርደት ያደርሱባቸው ነበር ፡፡ በዚህም ምክንያት በክርስቲያኖችና በቱርኮች መካከል የመስቀል ጦርነት ሊነሣ ችሏል ፡፡ የተሰተሰውም አንድ ጴጥሮስ የሚባል ባሕታዊ በየሀገሩ እየዞረ ብዙ ክርስቲያኖችን በመቀስቀስ የብረት መስቀሉን በትከሻው ተሸክሞ ተከታዮቹንም በልብሳቸው ላይ በተደሠሩት የመስቀል ትርጉም አስፋፍቶ ዘመተ ፡፡ ለጊዜው ባይተናወም በተደጋጋሚ በተደረገው ጦርነት በተለይ ጎድፍሬ በተባለው ፈረንሳዊ በተመራው ጦር ድል በመገኘቱ ኢየሩሳሌም ከ፲፻፺፱ ፲፩፻፳፯

ዓ/ም በክርስቲያኖች እጅ እንደነበረች የዓለም ታሪክ ይናገራል ፡፡

ከዚያም ወዲህ የተለያዩ መንግሥታት በሚያደርጉዋቸው ጦርነቶችና ምርኮዎች ምክንያት እያንዳንዱ ግማደ መስቀል በአራቱ ማዕዘናት ለ፬ ተከፋፍለው ሲወሰዱት አንዱን የቀኝ ክንፍ ግማደ መስቀል በአፍሪካ የነበሩ ክርስቲያኖች ወደ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አምጥተውት ለብዙ ዘመናት በዚያ (ተቀምጧል) ኖሮአል፡፡

ከዚያም አፄ ዳዊት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ብዙ መላላክ አድርገው ካስመጡት በኋላ በመሞታቸው ልጃቸው አፄ ዘርአ ያዕቆብ ሲነግሥ በደብረ ብርሃን ከተማ ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ ሊያስቀምጠው ሞክሮ ነበር ፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረምና በራዕይ "አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል" እያለ ስላመለከተው መስቀለኛ ቦታ በማስፈለግ በስሜን ወሎ በአምባሰል አውራጃ በሚገኘው በግሸን ተራራ ላይ ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ መስከረም ፳፩ ቀን ፲፬፻፵፱ ዓ/ም አስገብቶ በክብር እንዳስቀመጠው ታሪኩ በሰፊው ያብራራል ፡፡ በዚህም ቀን መስቀሉን ለማክበርና ለመሳለም ብዙ ክርስቲያኖች ከየሀገሩ ወደዚህ ቦታ እየተሰበሰቡ ሲያከብሩ ይኖራሉ ፡፡

በተለይ መስከረም ፲፯ ቀን ደመራ ደምረን ችቦ አብርተን የምናከብረው መስቀሉ እንደ ፀሐይ እያበራ ጨለማን የማራቁ ምሳሌ ሲሆን ደመራውም ዕሌኒ ንግሥት እጣን አቀጣጥላ በማጤስ መስቀሉን የማግኘቱ መታሰቢያ ነው ፡፡ ከዚህም ሌላ የክረምቱ ወራት አልፎ አበቦች የሚፈኩበት እሸቱ የሚደርስበት የፀሐይ

ብርሃን የሚደምቅበትና ፍጥረታት ሁሉ የሚደሰቱበት አዲስ ወራት በመሆኑ አበቦችን በደመራው እንጨት ላይ በማድረግና ችቦውን በማብራት በዓለ መስቀሉን በብርሃን መቀበላችን ነው ፡፡

በክርስቶስ መስቀል ኃይል ያገኙ ፡ ድል የተጐናፀፉ ፡ ከደዌአቸው የተፈወሱና ልዩ ልዩ ታምራት የተደረገላቸው ብዙዎችናቸው ፳ ሺ ከ፳ መቶ ዘመን ሙሉ በሲኦል ጨለማ ተውጠው የነበሩ ደቂቀ አዳም በመስቀሉ ብርሃን ወጥቶላቸዋል እርቀው ነበር ቀርበዋል ፡፡ በዕፀ በለስ ምክንያት ተሰነካክለው ወድቀው ነበር በዕፀ መስቀሉ ኃይል አግኝተው ተነሥተዋል ፡፡

ዛሬም በእምነት ጸንተው በጸበል ተጠምቀውና በመስቀል ተባርከው ፡ ከደዌ ኃጢአት የሚነጹ ፡ ከደዌ ሥጋ የሚፈወሱና ከርኩሳን አጋንንት (ቁራኛ) የሚላቀቁ ጥቂቶች አይደሉም ፡፡ የተለያዩ መጠመቂያ ቦታዎችን በምንጐበኝበትና መንፈሳዊ ጽሑፎችን በምናነብበት ጊዜ እንዲህ ዓይነቶችን ስንመለከት ክርስቲያን ለሆነ ሁሉ ታላቅ ተስፋ ነው ፡፡

ታዲያ መስቀሉንም ሆነ በዓሉን ስናከብር በዕለተ ዓርብ በመስቀሉ ላይ የፈሰሰውን ደም የተቆረሰውን ሥጋና ሕማማተ መስቀሉን እያሰብን አዳኝነቱንም በሚገባ ተረድተን በመቀበል መሆን አለበት ፡፡ ይህ ከሆነ አጋንንትን ድል እንነሣበታለን ሰላምንና በረከትን እናገኝበታለን ፡፡ ነገር ግን ምሥጢሩን ሳንረዳ የቅርጹን ማማር ብቻ በማየት ከወርቅ ፡ ከብር ፡ ከመዳብ ፡ ከነሐስ ፡ ከእብነ በረድና ከእንጨት እያሠራን መያዙና በአንገት ላይም ማሠሩ ለጌጥ

# የቆጋ ኪዳነ ምህረት ገዳም ታሪክ በአጭሩ

ታላቁ የቆጋ ኪዳነ ምህረት ገዳም የሚገኘው በጎጃም ሀ/ስብከት በሞጣ አውራጃ በጐንቻ ሲሶው እነብሴ ክልል ነው ፤ ገዳሙ የተቆረቆረው ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት መሆኑ ይነገራል በቀድሞ ዘመንም ሆነ አሁን መናንያን መነኮሳት መታወቅን ስለማይፈልጉ በአንዳንድ መንፈሳዊ ተግባርና ተአምር ምክንያት በሕዝብ ዘንድ መከበርንና መወደድን አገኙ፡፡

በተለይ ዓፄ ዓምደ ጽዮን በነገሡበት ዘመን ከ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ጀምሮ ይህ ገዳም በክርስቲያኖች ዘንድ መታወቅ ጀምሯል ስሙም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየገነነ ሄዷል ፤ በአፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ግራኝ መሐመድ በአካሄደው የክር

(ወደ ገጽ ፻ ዞሯል)

---

ነት እንጂ ለአዳኝነት አለመሆኑን መረዳት ይገባናል ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና" ባለው መሠረት ከልብ አምነን ለተቀበልነው ኃይላችን መጽናኛችን ፤ መዳኛችንና የነፍሳችን መድኃኒት ነው ፡፡

ስለዚህ መድኃኒታችን ክርስቶስ "ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ" በማለት ነፍሳችን ማዳን የምንችለው በዓለም ላይ የሚመጡብንን ሥጋዊ ፈተናዎች ታግሠን እሱን በግብር ለመከተል እንድንነሣ ያሳስበናል ፡፡

መ/መንክር ዋሴ



www.ethiopianorthodox.org

# ጻዕዳ አምባ ሥላሴና ታሪኩ

የጻዕዳ አምባ ሥላሴ ገዳም የተመሠረተው በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም ሲሆን የቆረቆሩትም ጻድቁ አቡነ ሰይፈ ሚካኤል ናቸው

ጻዕዳ አምባ ሥላሴ የሚገኘው በኤርትራ ክፍለ ሀገር በሰንሒት አውራጃ በሐጋዝ ወረዳ ከከረን ከተማ ምዕራብ ደቡብ ነው ።

ገዳሙን የቆረቆሩት አቡነ ሰይፈ ሚካኤልም የትውልድ ሀገራቸው በዚሁ ክፍለ ሀገር ሐማሴን አውራጃ አንሰባ ወረዳ ልዩ ስሙ (ዘርአ ሠናይ) ደርሰነይ ከሚባለው መንደር ከአባታቸው ከዓምደ ሚካኤል ከእናታቸው ከኂሩተ ማርያም በ፲፰፻፺፯ ዓ/ም ተወለዱ ። ለትምህርት ሲደርሱ ወላጆቻቸው በሚገባ እየተንከባከቡ ከማሳደጋቸው በላይ በመንፈሳዊ ትምህርት ታንጸው እንዲያድጉላቸውም ተማሪ ቤት አስገብተው አስተማርዋቸው

የመጻሕፍተ ብሉያትንና የመጻሕፍተ ሐዲሳትንም ንባብ ከእነትርጉሙ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ሐሳባቸው ሁሉ መንፈሳዊ ስለነበር ከተወለዱበት ክፈለ ሀገር ከኤርትራ ወደ ትግራይ ክፍለ ሀገር ሽሬ አውራጃ ውስጥ ወደሚገኘውና ዋላዊነ ኄር ተብሎ ወደሚጠራው ገዳም ገብተው አበውመነኮሳትን በመርዳት ከፍተኛ ተጋድሎ ሲፈጽሙ ከቆዩ በኋላ ትኅታቸወና ትሩፋታቸው ሁሉ በማኅበሩ ስለ ታወቀ የገዳሙ አበምኔት አቡነ ዕንቁ ብርሃን አመነኮሰዋቸው ከመነኮሱም በኋላ ወደ ዋልድባ ገብተው በጾም በጸሎት ተወስነው ሲኖሩ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ መጥቶ ትምህርት ሃይማኖትን የምታስፋፋበት ኢአማንያንን ወደ ቀናው ሃይማኖት የምትሰብበት ሌላ ቦታ አለና ወደዚያ ቦታ ሂድ አላቸው ፡ አቡነ ሰይፈ ሚካኤልም ይህንን ቃል ከመልአኩ ከሰሙ በኋላ ሳይውሉ ሳያድሩ ከዋልድባ ተነሥተው ወደ ኤርትራ ተመልሰው በሐማሴን አውራጃ ተግተውና ነቅተው ወንጌልን ያስተምሩ ጀምር ።

ወተፈወስት ምድረ ሐማሴን በምጽአቱ ለብፁዓዊ ሰይፈ ሚካ



የገዳሙ አፈ መምህር አባ ገብረ መስቀል

ኤል ይላል ገድላቸው ይኸም ማለት "ንዑድ ክቡር ሰይፈ ሚካኤል በመምጣቱ ምድረ ሐማሴን ዳነች" በዚህ መሠረት ከከረን ጀምሮ እስከ ሱዳን ድረስ ስብከተ ወንጌል ያልደረሰበት ስለ ነበር አቡነ ሰይፈ ሚካኤል አስተምረውና አሳምነው ጠቅላላ ሕዝቡን አጠመቁት ።

አቡነ ሰይፈ ሚካኤል በአቆርዳት አካባቢ ደብረ ሳለ የሚባለውን ገዳም መሥርተው የንፍሮና የአንድነት ማኅበር አቋቁመው ነበር ። ደብረ ሳላ ማለትም በበደው ቋንቋ ደብረ ጸሎት ማለት ነው ።

በዚህ ገዳም ለብዙ ዓመታት ከቆዩ በኋላ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ወደ ጻዕዳ አምባ እንዲሄዱ ነገራቸው ። ይህችም ጻዕዳ አምባ ሥላሴ በገደል የተከበበች መግቢያ የሌላት መሶብ መሰል ገደል ናት ።

ከአጠገብዋ ከባቦ የምትባል ተራራ አለች ከዚያችም ተራራ ፱ ዓመት ከ6 ወር ሲኖሩያች የተሰጠቻቸው ቦታ ሌሊት ሌሊት በአምደ ብርሃን ተከባ ትታያቸዋለች ቀን ቀን ሲያይዋት በእግር የማታስገባ በገደል የተከበበች ሁና ትታያቸዋለች ።

በዚህ ምክንያት እየተጨነቁ ሲኖሩ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ጸሎትህ ከእግዚአብሔር ፊት ደርሰአልና ደስ ይበልህ ይህች በአምደ ብርሃን ተከባ የምትታየትም ቦታ መካነ መቃብርህ ናት የልጆችህም ርስት ናት ስለ ዚህ አኔን ተከትለህ ና ብሎ አቡነ ሰይፈ ሚካኤልን እየመራ ከገዳሙ አድርሶ ተሠወራቸው አላቸውም በተደረገላቸው ተአምራት አምላካቸውን እያመሰገኑ ገዳምዋን በአራት መዓዝን ባረኳት ። ከዚህ በኋላ ሲባርኳት በዚያው አካባቢ የነበሩት መናፍስት ርኩሳን እያጮሁና እያለቀሱ እንደ ጢስ ተነው እንደ ትቢያም በነው ጠፉ።

አቡነ ሰይፈ ሚካኤልም በቅዱስ ገብርኤል አማካይነት ከገዳሙ ገብተው ሶስት ቀን ያህል ከሰነበቱ በኋላ ደቀ መዛሙርቶቻቸው አባታችን የት ጥለውን ሄዱ በማለት ያዝኑ ጀምር ። እመቤታችንም የእነሱን ሐዘንና ልቅሶ ተመልክታ አባታቸው ካሉበት ቦታ አድርሳ ከአባታቸው ጋር አገናኘቻቸው ። አቡነ ሰይፈ ሚካኤልም ልጆቻቸውን በማግኘታቸው በደስታ ላይ ደስታን በጸሎትም ላይ ጸሎትን በመጨመር ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ ።

የጻዕዳ አምባ ሥላሴ ገዳም መግቢያዋ የአንድ እግር ሜማ ካልሆነ በስተቀር ስፋት የሌላት ቀጭን ናት ይኸውም በአንዲት ቦታ ብቻ እንጂ በሌላ መግቢያ የላትም ። በቀኝ በግራ እጅግ የሚያስፈራ ገደል ነው ።

ገዳሙን አናያለን ብለው የሚሄዱትም ሰዎች አብዛኞቹ አሻግረው ከማየት በቀር ደፍሮ የሚገባ የለም ። አንዳንዶቹ ግን እየተኗቀቁ በብዙ ችግር ገብተው ገዳሙን አይተው ይመለሳሉ ።

ጻዕዳ አምባ ብዙ ተአምራት የሚፈጸምባት ገዳም ናት ። አቡነ ሰይፈ ሚካኤል በጻዕዳ አምባ ሥላሴ የአንድነት ማኅበር አቋቁመው ሥርዓተ ማኅበርንም አደራጅተው ካበቁ በኋላ የዕረፍታቸው ቀን ሲደርስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕረፍትህ ደርሶአል አላቸው። እሳቸውም ቃሉን በደስታ ከተቀበሉ በኋላ መቃብሬን ለሚጠብቁ ምን ዓይነት ዋጋ ትሰጣቸዋለህ ብለው ቢጠይቁት ስምህን የጠራ ፡ ቤተ ክርስቲያንህን ያሳነጸ በጸሎትህ ለተማፀነና መቃብርህን የጠበቀ ሁሉ አንተ ካገባህበት ውሳጤ መንጠላት ይገባል ሲል ቃል ኪዳን ከሰጣቸው በኋላ በ፺፯ ዓመታቸው አረፈዋል ።

በተሠጣቸውም ቃል ኪዳን መሠረት እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ አስደናቂ ኃይል እየታየ ነው ።

ለምሳሌ ገዳሙ ዙሪያው ሁሉ ገደል መሆኑን ጠቅሰነዋል ። ይሁን እንጂ በገደላገደሉ አፋፍ ታላላቅ ዋርካዎች አሉ ። የዋርካዎቹ ሥር ከላይ ሲሆን ቅርንጫፎቻቸው ግን ወደ ገደሉ የተንጠለጠሉ ስለሆኑ ቅጠላቸው ሁሉ ወደ ታች እንጂ ወደ ላይ አይታይም ።

ታድያ በገዳሙ ያሉት መነኮሳት ብቅል አብቅለው ጌሾ ወቅጠው እህል ቆልተው ጠላ አይጠምቁም ክብረ በዓል በሚሆንበት ጊዜ የረገፈውን የዋርካውን ፍሬ ሰብስበው ይጠነስስትና ጠላ የሚሆነው እሱ ብቻ ነው ከእሱ የሚጠመቀውም ጠላ ልክ በማር ወለላ የተጠመቀ እንጂ ከእንጨት ፍሬ የተጠመቀ አይመስልም መልኩም ቢሆን ንጹሕ ጠጅ እንጂ ጠላ አይመስልም ይህ ራሱ ታላቅ ተአምር ነው ።

በገዳሙ አካባቢ የሚገኙት ብሔረሰቦች ምንዓምር ፡ ብሌን ፡ ተብለው የሚጠሩ ናቸው ። በጻዕዳ አምባ ሥላሴ የሚገኙት መነኮሳት ምንም እንኳ በጾምና በጸሎት ተወስነው የሚኖሩ ቢሆኑም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእናንት ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ማቴ ፳፰ ፡ ፲፱ ባለው አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት እኛችን አጣምረን ዝም ብለን መኖር የለብንም ያልተማሩትን ማስተማር ያላመኑትም ማሳመን ግዴታ አለብን በሚል መንፈሳዊ አሳብ ቅዱስ ወንጌልን እንግበው ባጭር ታጥቀው ያደረጉት ጥረትና ሐዋርያዊ ተልዕኮ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ታንጸዋል ።

በጻዕዳ አምባ ሥላሴ መነኮሳት ትጋትና ጥረት የታነጹትም አብያታ ክርስቲያናት የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ. ከረን ልደታ ቅድስት ማርያም

፪ኛ. ሐጋዝ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

፫ኛ. ዓዲርዳዕአቡነ ተክለ ሃይማኖት

፬ኛ. አንገርኔ ቅዱስ ሚካኤል

፭ኛ. መንሱራ ቁስቋም ቅ·ማርያም

፮ኛ. አቁርዳት ኪዳነ ምሕረት

፯ኛ. ባረንቱ ቅዱስ ሚካኤል

፰ኛ. ተከምቢያ ደብረ ምጥማቅ ቅ·ማርያም

፱ኛ. ሐይኮታ መድኃኔ ዓለም

፲ኛ. ተሰነይ አስተርእዮ ማርያም

፲፩ኛ. ዓሊ ጊደር ቅዱስ ጊዮርጊስ

፲፪ኛ. ተላታ ዓሸር አቡነ ገ መንፈስ ቅ·

፲፫ኛ. ጋሎጅ ቅዱስ ገብርኤል

፲፬ኛ. እምሐጀር ቅዱስ ሚካኤል

፲፭. ተከዜ መድኃኔ ዓለም

፲፮ኛ. ጉጔ ኪዳነ ምሕረት ናቸው።

ስለዚህም ይህ በጻዕዳ አምባ የተደረገውና የታየው ሐዋርያዊ ተልዕኮ በሌሎችም ገዳማት ቢሠራ መልካም ነው እንላለን ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

## የቆጋ ኪዳ… ገዳም

(ከገጽ ፫ የዞረ)

ያደርጉ በተለይ በምግብ በኩል ራሳቸውን የቻሉ ናቸው ። እንዲያውም በተለያየ ወቅት በድርቅና በቸነፈር ምክንያት እያሌ ችግረኞችንና ስደተኞችን በመርዳት መንፈሳዊና ሰብአዊ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ

የቆጋ ኪዳነ ምህረት ገዳም አበምኔት መምህር ወ/ማርያም አየለ



www.ethiopianorthodox.org

## ወርኃ ጽጌያት

# ድንግል ማርያም በመንፈቀ ሌሊት

የተስፋ አጦች አለኝታ የችግረኞች ተስፋ የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሕፃንዋን ታቅፋ የአክስትዋ ልጅ ቅድስት ሰሎሜንና አረጋዊ ዮሴፍን አስከትላ ሰው ሳያያት ዘመድም ሆነ ባዕድ ሳይመለከታት በመንፈቀ ሌሊት ወደ ምድረ ግብጽ ተሰደደች ፤

ከዚሁ ላይ ሶስት ነገሮችን እንመለከታለን እነዚህንም ለምን እንደ ተፈጸሙ እንመረምራለን ፤

፩ኛ/ እመቤታችን ለምን ተሰደደች ?

፪ኛ/ ስደትዋ በቀን በብርሃን ሳይሆን ለምን በሌሊትና በጨለማ ሆነ ?

፫ኛ/ የእስያ ሀገር ሰፊና ለኢየሩሳሌም አካባቢ ቅርብ ሲሆን ለምን ወደ አፍሪካና ወደ ምድረ ግብጽ መሰደድን መረጠች ? በሚሉ ጥያቄዎች እናተኩራለን ። ለምን ተሰደደች ለሚለው ጥያቄ ሰብአ ሰገል በኮከብ እየተመሩ ኢየሩሳሌም ደረሱ በዚህ ጊዜ አይቴ ሀሎ ንጉሠ አይሁድ ዘተወልደ" የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የት ነው ብለው ሲጠይቁ ንጉሡ ሄሮድስ እጅግ ተጨነቀ ንጉሥማ ከተወለደ ንጉሥነን ሳይገድል ይነግሣልን በሚልም ሐሳብ እንቅልፍን አጣ ከዚህ በኋላ ለመሆኑ ኮከቡን ካያችሁበትና ሕፃኑ የተወለደበት ዘመን ስንት ይሆናል ሲል እንደገና ሰብአ ሰገልን ጠየቃቸው ። እነሱም ሁለት ዓመት ይሆናል ሲሉትና ዕድሜውን ካረጋገጠ በኋላ እንግዲህ ሳይቀድመኝ መቅደም አለብኝ ብሎ ምንም እንኳ ከየትኛው ጐሳ ከየትኛው ነገድ



ምስለ ፍቁር ወልዳ

እንደሆነ ለይቶ ባያውቀውም በቤተ ልሔምና በገሊላ አውራጃዎች የሚገኙትን ከ፪ ዓመት በታች ከ፩ ዓመት በላይ የሆኑትን ሕፃናት እንዲሰበሰቡ አዘዘ ፤ ትእዛዙም ደረቅ ትእዛዝ ሳይሆን ቀለብ ልብስ እሰጣለሁና ሕፃናቱን ሰብስቡልኝ በሚል ማታለያ ቃል ነበር፣ የገሊላ ሴቶችም ይህንን ቃል ሲሰሙ ልብስና ቀለብ የሚያገኙ መስሏቸው ለጆቻቸውን እያዘሉና እየታቀፉ ሁሉም በሄሮድስ ቤተ መንግሥት ተሰበሰቡ በዚህ ጊዜ ዓመፀኛው ሄሮድስ የገሊላና የቤተልሔም ሕፃናት በሙሉ እንደተሰበሰቡ ሲመለከት እንግዲህ ተወለደ የተባለው ንጉሥ ከእነዚህ መካከል አንዱ ሳይሆን አይቀርም በማለት ከዚያ የተሰበሰቡትን ሕፃናት በሙሉ አስፈጃቸው በዚያን ጊዜ በሄሮድስ ትእዛዝ ያለቁ ሕፃናት ከ፲፬ ሺህ (ከአሥራ አራት ሺህ) በላይ ነበር ። እግዚአብሔር ግን መልአኩን ልኮ ዮሴፍን ይህንን ሕፃንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ምድር ሽሽ ሄሮድስ ሊገድለው ይፈልገዋልና፣ ብሎ በሕልም ነግሮት ስለነበር አስቀድሞ የገሊላን ምድር ለቆ ወደ ግብጽ ስደቱን ቀጥሎ ነበር ስለዚህ እመቤታችን ልትሰደድ የቻለችው ልጇዋ እንዳይገደልባት ነው ። ስደትዋን ለምን በሌሊት አደረገችው ለሚለውም ጥያቄ መልሱ እንደሚከተለው ነው ።

በታሪክ እንደሚናገረው ያን ጊዜ ኢየሩሳሌም በሮማውያን ጽኑ አገዛዝ ትገዛ ስለነበርና እሥራኤላውያንም አስከፊና አሰቃቂ ከሆነው ከሮማውያን አገዛዝ የተነሣ ሰው ሳያያቸው በገደላገደል እየተንጠላጠሉ ቅጠሉን ለብሰው ጨለማውንም ተገን አድርገው ከማምለጥ በስተቀር ሌላ ዕድል ስላልነበራቸው ሁሉም ወደ ግብጽ ይሸሹ ነበር ምክንያቱም መንገዶች ሁሉ ተዘግተው ዙርያውንም በሮማውያን ወታደሮች ተከቦ ስለነበር ከውጭ የሚገባ ከውስጥም ወደ ውጭ የሚወጣ አልነበረም ።

እመቤታችንም በመንፈቀ ሌሊት የወጣችውና ስደትዋን በሌሊት ያደረገችው በሌላ ሳይሆን በቀን የሄድኩ እንደሆነ ሰዎች ያዩኛል የሮም ወታደሮችም ያዩኝ እንደሆነ ያስሩኛል ሰው ሲወጣ ሲገባ ያሥሩ ነበርና ስለዚህ ነው ከኢየሩሳሌም በመንፈቀ ሌሊት ወጥታ ወደ ግብጽ ልትሰደድ የቻለችው ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢሮዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ.
የመልእክት ሣ.ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org